# Public Consultation toward Ethiopia's Family Law Reform and the Revised Code's Response

**DOI** http://dx.doi.org/10.4314/mlr.v10i1.8

Mandefrot Belay♣

## Summary

A comprehensive and open public consultation was conducted during the revision process of the Ethiopian family law (in 1998-2000) which attracted active participation from different sections of the Ethiopian society. Various issues were raised by members of the public in the process of reforming Ethiopia's family law. This note provides the historical context and background of the reform initiative and the outcome thereof. The note identifies the issues that were subject of discourse and shows how the current law has addressed them. It can indeed inspire further research in the field by putting in perspective the fundamental values and principles in Ethiopia which are expected to guide any legal reform process so that the intervention of the law can address societal problems.

The core controversial issues raised in the various consultation forums were presented for final discussion at the concluding July 1999 conference held in Addis Ababa before the final draft was submitted. Such public participation in the legislative process was unprecedented. This note provides brief analysis of the main issues raised by the public, the views of the main stakeholders about the existing law, the way in which public consultation forums were organized, and the roles played by different sections of the society in advancing the respective values which they believe must be incorporated in the new family law.

The note lists down specific questions and the arguments raised by the public as to why the new family law should or should not be framed in a particular way, and it also shows the ultimate option adopted by the legislature in the final enacted version of the law. The core issues discussed in the note, *inter alia*, include the pros and cons of having a uniform family law, the various forms and impediments to marriage, the desirability of maintaining irregular union in the new code, betrothal, the institution of family arbitration and grounds of divorce. We believe this note will help researchers, law students and the general public in understanding the background and legislative intent behind the various provisions of the current revised family code, i.e. the 2000 Revised Family Code of Ethiopia.

♣ Mandefrot Belay (LL.B, LL.M), Consultant and Researcher. Formerly: Country Director, American Bar Association Rule of Initative, Ethiopia Legal Education Capacity Building Program; Directror of the National Justce Sector Reform program, Ministry of Capacity Building;Head of the Law Reform Bureau, at the Justice & Legal Systems Research Institute.

# የኢትዮጵያን የቤተሰብ ሕግ በማሻሻል ሂደት ከኅብረተሰቡ የተነሱ ጥያቄዎች፣ አከራካሪ ጭብጦችና የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ምላሽ

ማንደፍሮት በላይ*

## መግቢያ

በአገራችን በ1952 የወጣው የፍትሐብሔር ሕግ አካል የነበረው የቤተሰብ ሕግ መሠረት ያደረገው በአብዛኛው በወቅቱ የነበረውን የኅብረተሰቡን የእድገት ደረጃ፣ አስተሳሰብና አመለካከት እንደነበር ግልጽ ነው። ምንም እንኳን በቤተሰብ ሕጉ የተካተቱ የተለያዩ ጉዳዮችና አስተሳሰቦች በሙሉ ጊዜ ያለፈባቸው ናቸው ማለት ባይቻልም ከሕገ መንግሥቱ ዓላማና ይዘት እንዲሁም አሁን ካለው ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብና ኅብረተሰባችን ከደረሰበት የእድገት ደረጃ አንፃር መለወጥና ማሻሻል አስፈላጊ በመሆኑ የቤተሰብ ሕግ ተሻሽሏል።

የቤተሰብ ሕጉን ለማሻሻል ሲታሰብ በመጀመሪያ የተነሳው ጥያቄ ራሱን የቻለ አዲስ የቤተሰብ ሕግ በመደንገግ በኮድ (Code) መልክ ማውጣት ያስፈልጋል ወይስ በነባሩ የፍትሐብሔር ሕግ ላይ ማሻሻያ ማድረግ የሚል ነበር። ይህን ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችል ጥናት በፍትሕና ሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት በተቋቋመ የጥናት ቡድን ከተካሄደ በኋላ አማራጭ ሓሳቦችን የያዘ ጥናት ቀርቦ በነበሩ የፍትሐብሔር ሕግ ላይ ማሻሻያ አዋጅ ከማውጣት ይልቅ ራሱን የቻለ አዲስ የቤተሰብ ሕግ በኮድ መልክ ቢወጣ እንደሚሻል ተወሰነ። በዚህም መሠረት በ1952 ዓ.ም የወጣው የፍትሐብሔር ሕግ አካል የነበረውን የቤተሰብ ሕግ በተለይ ራሱን ችሎ እንዲወጣ ለማድረግ የማሻሻል ሥራው ሰፊ የሕዝብ ተሳትፎን ባካተተ ሁኔታ ተከናውኗል።[1]

የዚህ ጽሁፍ ዓላማ ሕጉን በማሻሻሉ ሂደት የተደረገው ሕዝባዊ ተሳትፎ እንዴት እንደነበር፣ የሕዝብ ተመራጮች፣ የሕግ ባለሙያዎች፣ ሌሎች የማህበራዊ ሳይንስ ምሁራን፣ ማህበራትና ሌሎች ልዩ ልዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ያነሷቸው ጥያቄዎችና አካራካሪ ጭብጦች ምን እንደነበሩና በመጨረሻ ተሻሽሎ በአዲስ መልክ የወጣው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ ያስገኘውን ምላሽ በአጭሩ በማቅረብ ወደፊት ሕጉን በመተግበሩ ሂደት በልዩ ልዩ የሕጉ አንቀጾች ላይ ሊነሱ ለሚችሉ የተለያዩ ጉዳዮች ቅድመ መነሻቸው (background) ምን እንደነበረ ማሳየትና በቀጣይ ለሚካሄዱ ጥናትና ምርምሮች መነሻና አጋዥ እንዲሆን ማድረግ ነው።

## 1. የቤተሰብ ሕግን ለማሻሻል ሓሳብ ለማሰባሰብ የተካሄዱ ዐውደ ጥናቶች

ቤተሰብ የኅብረተሰብ የተፈጥሮ መሠረታዊ መነሻ በመሆኑ ከኅብረተሰቡና ከመንግሥት ጥበቃና እንክብካቤ የማግኘት መብት እንዳለው በሕገመንግሥቱ የተደነገገ መሆኑ ይታወቃል። መንግሥትም ይህን ሃላፊነት ለመወጣትና ባጠቃላይ የዜጐችን መብት ለማስከበር ባለበት ኃላፊነት አስፈላጊ ሕጐችን በማውጣት፣ በማሻሻልና የአፈፃፀም ሥልቶችን በመቀየስ መሥራት እንዳለበት ግልጽ ነው። በተለይም አዲስ የሚወጣው የቤተሰብ ሕግ የተጋቢዎችን መብቶች በአግባቡ የሚያስጠብቅና ተቀባይነት ያላቸውን ሀይማኖታዊና ባህላዊ እሴቶችን የሚያካትት

* የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ ከ1990-1994 ዓ.ም በፍትሕና ሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት የሕግ ጥናት፣ ምርምርና ማሻሻያ ቢሮ ኃላፊ በመሆን የቤተሰብ ሕግን ጨምሮ ሌሎች ዋና ዋና የፌዴራል ሕጎችን የማሻሻል ሥራ በኃላፊነት የመሩ ሲሆን፣ ቀጥሎም ከ1994-1999) በፌዴራል መንግሥት የተደራጀው አገር አቀፍ ፍትሕ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም ዳይሬክተር በመሆን የሠሩ ናቸው። በአሁኑ ጊዜ የግል አማካሪና ተመራማሪ ናቸው።

[1] ከፌዴራል እስከ ክልል የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን የማወያየቱና ሀሳብና አስተያየት የማሰባሰቡ ሥራ በተከታታይ ለስምንት ወራት የተካሄደ ሲሆን፤ ይህም በአንጻራዊት ረጅም ጊዜን የፈጀና በልዩ ልዩ መልክ የተደራጁም ያልተደራጀም የህብረተሰብ ክፍሎችን ያሳተፈና ውጤታማ ነበር ማለት ይቻላል።

መሆኑን ማረጋገጥ እንዳለበት ባለሙያዎች አበክረው ተከራክረዋል፡፡ ከዚህ በላይ እንደተገለፀው የቤተሰብ ሕግ በቅድሚያ ተሻሽሎ መውጣትና በሥራ ላይ መዋል ያለበት መሆኑ ስለታመነበት የመወያያ ረቂቅ በቅድሚያ በፍትሕ ሚኒስቴር ተዘጋጅቷል። በረቂቁ ሕግ ውስጥ በዝርዝር የተካተቱት ጉዳዮች የኅብረተሰብ መሠረት የሆነውን ቤተሰብ በአጠቃላይና የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን፣ ልዩ ልዩ የፌዴራልና የክልል መንግሥት አካላትን የሚመለከት በመሆኑ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ተሳትፎ በእጅጉ አስፈላጊ ነበር፡፡

ስለሆነም የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችና ተቋማት ተሻሽሎ በሚወጣው የቤተሰብ ሕግ ውስጥ ሊካተቱ የሚገባቸው አስተሳሰቦችና ጠቃሚ ባህላዊና ሀይማኖታዊ እሴቶች ምን መሆን እንዳለባቸው እንዲሁም መወገድ ያለባቸው ጎጂ ልምዶች የትኞቹ እንደሆኑ በጥልቀት ተወያይተው አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ለማድረግ የሚያስችሉ ለስምንት ወራት ያህል ጊዜ የቆዩ የተለያዩ ዐውደ ጥናቶችና የውይይት መድረኮችና ሰፋ ያሉ አገር አቀፍ ኮንፍረንሶች ተካሂደዋል፡፡ ከኅዳር ወር 1991 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ ወር 1991 ዓ.ም ድረስ በቆየው የምክክርና ውይይት ጊዜ ሰፋ ያለ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ያሳተፉ ስድስት አውደ ጥበባቶችና የውይይት መድረኮች ተካሂደዋል፡፡ በነዚህ መድረኮች ላይ በተደረጉ ውይይቶችም ሰፊ የአስተሳሰብና የአመለካከት ልዩነቶች የተንጸባረቀባቸው አስተያየቶችን ለማሰባሰብ ተችሎ ነበር፡፡ ይህም ከ1983 ዓ.ም የመንግሥት ለውጥ በኂላ ከተደረጉ የሕግ ማውጣትና ማሻሻል ሥራዎች ከሕገመንግስቱ ቀጥሎ ከፍተኛ የሕዝብ ተሳትፎ የተደረገው የቤተሰብ ሕግን ለማሻሻል በተደረገው እንቅስቃሴ ነበር ማለት ይቻላል፡፡[2]

በዚህ መሠረት፣

ሀ) በኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የሴቶች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ አስተባባሪነትና በፍትህና ሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት ሞያዊ ድጋፍ ከሕዳር 23-25 ቀን 1991 ዓ.ም. በደብረዘይት የሥራ አመራር ኢንስቲትዩት ቁጥራቸው ከ150 በላይ የሆኑ በክልልና በማዕከል በየደረጃው የሚገኙ ሴት ተመራጮችና ሌሎች ተጋባዥ እንግዶችና ባለሙያዎች የተሳተፉበትና ለአራት ቀናት የቆየ አውደ ጥናት ተካሂዷል፡፡ በዚህ አውደ ጥናት ላይ በ1952 ዓ.ም. በወጣው የኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሕግ ውስጥ የቤተሰብ ሕግን በተመለከተ በልዩ ልዩ ምዕራፎች ከሰፈሩት ድንጋጌዎች መካከል ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገባና ውይይት የሚያስፈልጋቸው ዋና ዋና ጉዳዮች ተመርጠው አራት የመወያያ ጥናታዊ ጽሁፎች ተዘጋጅተው ቀርበዋል፡፡ የመወያያ ጽሁፎቹ በጋብቻ አፈፃፀም፣ ከጋብቻ ውጭ የሚደረጉ ግንኙነቶች ስለሚያስከትሏቸው ውጤቶች፣ ስለጋብቻ መፍረስ፣ ስለመወለድና የጉዲፈቻ ውል በሚሉ ርዕሶች ላይ የተደረጉ ጥናቶች ነበሩ፡፡

ለ) በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት የሴቶች ጉዳይ ንዑስ ዘርፍ አስተባባሪነትና በፍትህና ሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት ሙያዊ ድጋፍ ከጥር 24-28 ቀን 1991 ዓ.ም. ድረስ በአዲስ አበባ ከተማ የአምስት ቀን አውደ ጥናት ተካሂዷል፡፡ በዚህ አውደ ጥናት ከላይ በተራ ቁጥር አንድ የተገለፁት ጥናታዊ ጽሁፎች በድጋሚ የቀረቡ ሲሆን በቤተሰብ ሕጉ ረቂቅ ላይም በቡድንና በጋራ ውይይቶች ተደርገዋል፡፡ የአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎችም በተለያዩ ማህበራት የተደራጁ ሴቶችና የሌሎችም አካላት ተወካዮች ነበሩ፡፡ በዚህም መሠረት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ሠራተኛ ሴቶች፣ ነጋዴ ሴቶች፣ በልማት ማህበራት የተደራጁ ሴቶች፣ በሙያ ማህበራትና በሌሎችም ማህበራት የተደራጁ ቁጥራቸው 250 የሚደርሱ ተወካዮች ተሳትፈው ነበር፡፡

ሐ) በአዲስ አበባ መስተዳደር ም/ቤት አስተባባሪነት ከመጋቢት 26 እስከ 27 ቀን 1991 ዓ.ም. ድረስ ቁጥራቸው ከ200 በላይ የሚሆኑ ከመስተዳድሩ ምክር ቤት ጀምሮ በዞን፣ በወረዳና በቀበሌ የሚገኙ የአመራር አባላት፣ በመስተዳድሩ የተለያዩ የሴክተር መ/ቤቶች ተወካዮች፣

[2] የወንጀል ሕጉ ሲሻሻል የነበረው የሕዝብ ተሳትፎ ከቤተሰብ ሕጉ ቀጥሎ ከፍተኛው ነበር፡፡

ከየወረዳው የተወከሉ የከተማዋ ነዋሪዎች፣ ታዋቂ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የሴቶችና የወጣቶች ማህበራት ተወካዮች ተሳታፊ የሆኑበት የሦስት ቀናት ዐውደ ጥናት ተካሂዷል። በዚሁ ዐውደ ጥናት ላይ ከጋብቻ ውጭ በግብረ ሥጋ ግንኙነት አብሮ መኖር ስለሚያስከትላቸው ውጤቶች፣ የጉድፈቻ አገልግሎት በኢትዮጵያ፣ የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ሥርዓት ምንነት፣ ሥርዓቱን የመዘርጋት አስፈላጊነትና አሠራር በሚሉ ርዕሶች ላይ ለውይይት መነሻ የሚሆኑ ሦስት ጽሁፎች የቀረቡ ከመሆኑም በላይ ለውይይት በተዘጋጀው የቤተሰብ ሕግ ረቂቅ ላይ ሰፊ ውይይት ተካሂዷል።

መ) በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አስተባባሪነትና በፍትህና ሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት ሙያዊ ድጋፍ ከሚያዝያ 18 እስከ 22 ቀን 1991 ዓ.ም. ድረስ ቁጥራቸው ከሁለት መቶ በላይ የሚሆኑ የተለያዩ የሀይማኖቶች ተወካዮች፣ የሠራተኛና የሙያ ማህበራት፣ አገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ አግባብ ያላቸው የፌዴራል መ/ቤቶችና የክልል ቢሮዎች ተወካዮች እንዲሁም ታዋቂ ምሁራንና ግለሰቦች የተሳተፉበት የአምስት ቀናት አውደ ጥናት በአዲስ አበባ ከተማ ተካሂዷል። በዚሁ ዐውደ ጥናት ላይ የቤተዘመድ ሽምግልናና የምክረ ትዳር አገልግሎት ንጽጽር፣ የቤተሰብ መፍረስ በሕፃናት ላይ የሚያደርሰው ችግርና የጉዲፈቻ አገልግሎት እና በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና የወሳኝ ኩነቶች መረጃ ሥርዓት በሚሉ ርዕሶች ላይ ሦስት ጥናታዊ ጽሁፎች የቀረቡ ከመሆኑም በላይ በረቂቅ የቤተሰብ ሕጉ ላይ በቡድንና በተሳታፊዎች በአጠቃላይ ሰፊ ውይይት ተካሂዷል።

ሠ) ከግንቦት 23 እስከ 25 ቀን 1991 ዓ.ም. ደግሞ በድሬዳዋ አስተዳደር የሚገኙ ቁጥራቸው ከሁለት መቶ ሀምሳ በላይ የሚደርስ በተለያየ ደረጃ የሚገኙ የመስተዳድሩ አመራር አካላት፣ የሀይማኖት ተወካዮች፣ ማህበራት፣ የከተማና የገጠር ቀበሌዎች ነዋሪዎች ተወካዮች፣ በአጠቃላይ በአስተዳደር ክልሉ የሚገኙ ልዩ ልዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች የተሳተፉበት የሦስት ቀናት ኮንፍረንስ በድሬዳዋ ከተማ የተካሄደ ሲሆን በኮንፍረንሱ ላይ ለውይይት መነሻ የሚሆኑ ጽሁፎች ከቀረቡ በኋላ በረቂቅ የቤተሰብ ሕጉ ላይ ሰፊ ውይይት ተካሂዷል። የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ስርዓት አስፈላጊነት፣ ከጋብቻ ውጭ አብሮ ስለመኖርና የቤተዘመድ ሽምግልና ጉባኤን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ለውይይት መነሻ የሚሆኑ ጽሁፎች ቀርበው ውይይት ተካሂዷል።

ረ) ከሰኔ 21-25፣ 1991 ዓ.ም ደግሞ ከኅዳር ወር ጀምሮ በአገር አቀፍ ደረጃ ረዘም ላሉ ወራት ሲካሄድ የቆየው ምክክር ማጠቃለያ የሆነ ከ200 በላይ ተሳታፊዎችን ያካተተ አገር አቀፍ ኮንፍረንስ አዲስ አበባ ውስጥ በተባበሩት መንግሥታት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን አዳራሽ ለሁለት ቀናት ተካሂዶ ነበር። በዚህ ኮንፍረንስ ቀደም ባሉት ጊዜያት ተነስተው የነበሩ አከራካሪ ጭብጦችና የተጠቆሙ የማሻሻያ የመፍትሔ ሓሳቦች ተገምግመዋል። ይህ የመጨረሻው አገር አቀፍ ኮንፍረንስ የተሻሻለው ረቂቅ ለሚኒስተሮች ምክር ቤትና ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከመቅረቡ በፊት የተደረገና በየአውደ ጥናቶች በተደረጉ ውይይቶች የተሰበሰቡ ሓሳቦችን በማዳበርና በተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች የተነሱትን ጥያቄዎች በማጤን ተቀባይነት ያለው የተሻሻለ የመጨረሻ ረቂቅ ለማቅረብ የታለመ ነበር።[3]

[3] በአጠቃላይ ኅብረተሰቡን ለማሳተፍ በተደረገው ጥረት በልዩ ልዩ መገናኛ ዘዴዎች ማለትም በጋዜጦች፣ በሬዲዮና በቴሌቭዥን ስርጭት የተከታተለውን ሳይጨምር መደበኛ (formal) በሆኑ የውይይት መድረኮች አማካኝነት ቁጥራቸው ከአንድ ሺህ ሁለት መቶ ሀምሳ በላይ የሆኑ በልዩ ልዩ የሙያ፣ የትምህርትና የሥራ ደረጃ ላይ የሚገኙ በርካታ የኅብረተሰብ ክፍሎችን የሚወክሉ ሰዎች በቀጥታ ተሳትፈዋል። ይህም በሕጉ ላይ ሰፊ ግንዛቤ ለመፍጠርና በአንዳንድ ጭብጦች ላይ በጣም የተራራቁ አስተሳሰቦችን ለማቀራረብ አስችሏል።

## 2. ስለሕጉ ወጥነት፣ስለጋብቻ አፈፃፀምና መተጫጨት የተነሱ ሓሳቦች

ከላይ እንደተገለፀው ከኅዳር ወር 1991 ጀምሮ በተከታታይ ለስምንት ወራት በተደረጉትና ልዩ ልዩ አካላትና የኅብረተሰብ ክፍሎች በተሳተፉባቸው ዐውደ ጥናቶች ከቀረቡት ጥናታዊ ጽሁፎችና በረቂቁ ላይ በተደረጉ ውይይቶች የተለያዩ አስተሳሰቦች የተንፀባረቁ ከመሆኑም በላይ በርካታ አከራካሪ ጉዳዮች ተነስተው ነበር፡፡ እነዚህ አከራካሪ ናቸው የተባሉት ጭብጦች ብዙ ክርክር ያስነሱና ሰፊ የሓሳብ ልዩነት የታየባቸው፣ እንዲሁም በተግባር ላይ ችግር አስከትለዋል ወይም ሊያስከትሉ ይችላሉ በተባሉ ጉዳዮች ላይ የተነሱት በአንደኛ ደረጃ የሚታዩት ጭብጦች ምድብ አንድ በሚል የተመዘገቡ ሲሆን፤ በሚያስነሱት ክርክር በደረጃ ከነዚህ ቀጥሎ መጠነኛ የሓሳብ ልዩነት ያስከተሉ ጉዳዮች ደግሞ ምድብ ሁለት ተብለው በደረጃ ተከፍለው እንዲመዘገቡ ተደርገዋል፡፡ በዚህ ጽሁፍ የቀረቡት ዋና ዋና የተባሉትና ሰፊ የሓሳብ ልዩነት የታየባቸው ናቸው፡፡

### 2.1 አንድ ወጥ የቤተሰብ ሕግ ወይስ ለየክልሉ የተለያየ ሕግ

በመጀመሪያ የቤተሰብ ሕጉን ለማሻሻል ጥናት ሲጀመር የተነሳው ጥያቄ በአሁኑ ጊዜ በአገሪቱ የሚያስፈልገው አንድ ወጥ የቤተሰብ ሕግ ወይስ በየክልሉ የተለያየ ሕግ የሚለው ጉዳይ ነበር፡፡ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት መሠረት የመንግሥት ሥልጣን በፌዴራል መንግሥትና በክልሎች መካከል የተከፋፈለ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በፌዴራል መንግሥት የሥልጣን ክልል ሥር ባሉ ጉዳዮች ሕግ የማውጣት ሥልጣን የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት መሆኑ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 55/1 የተደነገገ ሲሆን ምክር ቤቱ ዝርዝር ሕግ ሊያወጣ የሚችልባቸው ጉዳዮችም በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር ተዘርዝረዋል፡፡ በዚህም መሠረት የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት አንድ ወጥ የንግድ ሕግ፣ የወንጀል ሕግና የሠራተኛ ጉዳይ ሕግ እንደሚያወጣ የተገለፀ ሲሆን በአንጻሩ ክልሎች የክልል ሕገመንግሥትን ጨምሮ ሌሎች የፍትሐብሔር ሕጎችን እንደሚያወጡ ተደንግጓል፡፡ የቤተሰብ ሕግን በሚመለከት በግልጽ የተደነገገ ነገር የለም፡፡ ይሁን እንጂ የቤተሰብ ሕግ በፍትሐብሔር ሕግ ውስጥ ሊመደብ የሚችል በመሆኑ ክልሎች ከራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት የራሳቸውን ሕግ ሊያወጡ ይችላሉ የሚል እምነት አለ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 62/8/ መሠረት የፌዴሬሽን ም/ቤት በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ሕግ ሊወጣላቸው የሚገባ የፍትሐብሔር ሕጎችን ለመለየት ሥልጣን ያለው በመሆኑና በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 55/6 [4] መሠረት አንድ የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ለመፍጠር ሲባል በፌዴራል መንግሥት ሕግ እንዲወጣላቸው በፌዴሬሽን ም/ቤት በታመነባቸው የፍትሐብሔር ጉዳዮች የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ሕግ ሊያወጣ የሚችል በመሆኑ የቤተሰብ ሕግም በዚህ መንፈስ ታይቶ በሁሉም ክልሎች በአንድ ወጥነት የሚሠራበት የቤተሰብ ሕግ መደንገግ ይኖርበታል የሚል አመለካከት ነበር፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ደግሞ በየክልሉ የተለያየ የቤተሰብ ሕግ ማውጣት የሕጎች ግጭት ሁኔታን ስለሚፈጥርና በአፈፃፀም ችግር ሊያስከትል ስለሚችል አንድ ወጥ ሕግ ማውጣቱ ጠቀሜታው የጐላ ነው የሚል አመለካከት ነበር፡፡

ከዚህ ለየት ባለ ሁኔታ ደግሞ የቤተሰብ ሕግ የማውጣት ሥልጣን ለክልሎች የተተወ ነው ሊባል ቢችልም እንደ አዲስ አበባና ድሬዳዋ ያሉት ከተሞችና አካባቢዎች በፌዴራል መንግሥት የሚተዳደሩ በመሆኑ ለእነዚህ አካባቢዎች የፌዴራሉ መንግሥት የቤተሰብ ሕጉን በማውጣት በነዚህ ቦታዎች ተግባራዊ ማድረግና ሌሎች ክልሎች ይህን የፌዴራል ሕግ እንደ ሞዴል ተጠቅመው የራሳቸውን ሕግ ሊቀርጹ ወይም ሕጉን በኮንቬንሽን መልክ እንዳለ ሊቀበሉ

[4] በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 55(6) መሠረት አንድ ወጥ ሕግ ሊወጣላቸው ይገባል ተብለው ከተለዩት ጉዳዮች በፍትሕና ሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት ተዘጋጅቶ ቀርቦ ያለ ብዙ ችግር የፌዴሬሽን ምክር ቤት ይሁንታን በማግኘት የወጣው ሕግ የሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ አዋጅ ነው፡፡

የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር ይቻላል የሚል አመለካከት በሰፊው ተንፀባርቋል፡፡[5] በተለያዩ መድረኮች ጥያቄው እየቀረበ ክርክሮች ተደርገውበታል፡፡ ይህ አንድ ወጥ የቤተሰብ ሕግ በፌዴራል ደረጃ የመደንገጉ አስፈላጊነት በተለያዩ ወገኖች የታመነበት ቢሆንም በሕገመንግሥቱ ከተደነገገው የሕግ ማውጣት ሥልጣን ክፍፍልና በየክልሉ ካለው ባህላዊና ሀይማኖታዊ ሁኔታዎች አንፃር ታይቶ በመጨረሻ ለምክር ቤት የቀረበውና የፀደቀው ሕጉ በፌዴራል መንግሥት ሥር ባሉት ከተሞች ብቻ ተፈፃሚ እንዲሆን ተደርጐ ነው፡፡ ሕጉ ከፀደቀ በኋላ በማሻሻያው ሥራ ሂደት ተነስቶ የነበረው የሕጉ በኮንቬንሽን መልክ በክልል ተቀባይነት ጉዳይ አልተገፋበትም፡፡ በአንፃሩ ክልሎች የየራሳቸውን ሕግ በአዲስ መልክ ለማውጣት ባደረጉት እንቅስቃሴ የፌዴራሉን ሕግ ዋና መነሻና መረጃ (reference) አድርገው ተንቀሳቅሰዋል ማለት ይቻላል፡፡

## 2.2 ስለ ጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓት (Forms of marriage)

የጋብቻ አፈፃፀምን በተመለከተ የተነሳው አከራካሪ ጥያቄ አዲስ በሚወጣው የቤተሰብ ሕግ ውስጥ መካተት ያለበት አንድ ዓይነት የሆነ የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓት /የብሔራዊ ጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓት/ ወይስ ሀይማኖታዊና ባህላዊ የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓቶችም በዚሁ ሕግ ተካተው መውጣት አለባቸው የሚለው ነበር፡፡ በነባሩ የፍትሐብሔር ሕግ መሠረት ጋብቻ በሦስት ዓይነት የአፈፃፀም ሥርዓት ማለትም በብሔራዊ ጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓት፣ በሀይማኖት ሥርዓትና በባህላዊ ሥርዓት ሊፈፀም ይችላል፡፡ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 34/4/ መሠረትም በሕግ በተለይ በሚዘረዘረው መሠረት በሀይማኖትና በባህል የሕግ ሥርዓቶች ተመሥርተው ለሚፈፀሙ ጋብቻዎች እውቅና ሊሰጥ የሚችል ሕግ ሊወጣ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡

እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 34/4/ የተጠቀሰውና በሀይማኖትና በባህል የሕግ ሥርዓቶች ለሚፈፀሙ ጋብቻዎች እውቅና ሊሰጥ የሚችለው ሕግ ይህ የቤተሰብ ሕግ መሆን አለበት ወይስ የተለየ ሕግ የሚለው ነው፡፡ በዚህ ጥያቄ ላይ የነበረው አስተሳሰብ ሁለት ዓይነት ነው፡፡ አንደኛው አመለካከት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 34/4/ መሠረት ሊወጣ የሚችለውን ሕግ ሀይማኖታዊና ባህላዊ እምነቶችን መሠረት አድረጐ በሀይማኖት ወይም በልማድ የሚፈፀመው ጋብቻ ማሟላት የሚገባቸውን መሥፈርቶች በሚዘረዝር መልኩ በተለየ ሁኔታ የሚወጣ ሲሆን ከዚህ የቤተሰብ ሕግ የተለየ ነው የሚል ነው፡፡

ሁለተኛው አመለካከት ደግሞ ለሀይማኖታዊና ባህላዊ ጋብቻዎች እውቅና የሚሰጠው ሕግ ጋብቻው ዕውቅና እንዲያገኝ መሟላት ያለባቸውን መሠረታዊ ሁኔታዎች የግድ መደንገግ ይኖርበታል፤ እነዚህ ሁኔታዎች ደግሞ በሕገ መንግሥቱ የተደነገጉ መሠረታዊ መብቶችና መርሆዎችን የሚመለከቱ መሆን ይኖርባቸዋል፤ ለምሳሌ ጋብቻው በተጋቢዎች ሙሉና ነፃ ፈቃድ የተመሠረተ መሆኑ፣ ወንዱና ሴቲቱ በጋብቻ አፈፃፀም በጋብቻ ጊዜና በፍቺ ጊዜ እኩል መብት ያላቸው መሆኑን፣ ሴቶችን የሚጨቁን ወይም በአካላቸው ወይም በአዕምሮአቸው ላይ ጉዳት የማያስከትል መሆኑንና ሌሎች በሕገ መንግሥቱ የተዘረዘሩ መብቶችን የሚያስከብር መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል፤ እውቅና ሰጭው ሕግ ይህን መሰል ይዘት የሚኖረው ከሆነ ደግሞ በሀይማኖት ሥርዓትም ሆነ በባህል የሚፈፀሙ ጋብቻዎች በይዘታቸው ከብሔራዊ ጋብቻ የሚሉት በጋብቻው አከባበር ላይ ብቻ ስለሚሆን የተለየ ሕግ ማውጣት ሳያስፈልግ ሁሉንም በቤተሰብ ሕግ ውስጥ ማጠቃለል ይቻላል፤በተጨማሪም ጋብቻን በብሔራዊ ጋብቻ አፈፃፀም ደንብ በክብር መዝገብ ሹም ፊት ማድረጉ አስፈላጊ የሆኑ የጋብቻ ሁኔታዎች ማሟላታቸውን በቀላሉ ለመቆጣጠርና ከጐጂ ልምዶች ቤተሰብና ጋብቻን ለመጠበቅ ይረዳል የሚል ነው፡፡

ከዚህ ትንሽ ለየት ብሎ የሚታየው አመለካከት ደግሞ በእርግጥ የጋብቻ ሁኔታዎች በማናቸውም ዓይነት የጋብቻ አፈፃፀም መከበር እንዳለባቸው ግልጽ ቢሆንም አፈፃፀማቸውን በተመለከተ ሁሉም ጋብቻ በብሔራዊ ጋብቻ አፈፃፀም ደንብ ይደረግ ማለቱ አስቸጋሪ ስለሚሆን

---

[5] ሴት ተመራጮች በዋናነት በተሳተፉባቸው አገር አቀፍ ኮንፍረንሶችና ዐውደ ጥናቶች የሚያስፈልገው አንድ ወጥ የቤተሰብ ሕግ ወይስ በየክልሉ የተለያየ ሕግ የሚለው ጉዳይ በሰፊው ያከራከረና አንድ ወጥ የቤተሰብ ሕግ ቢወጣ ይሻላል የሚለው አመለካከት ጎልቶ ይታይ እንደነበር መታዘብ ይቻላል፡፡

ተጋቢዎች ከፈለጉ ጋብቻውን በሀይማኖታቸው ወይም በባህላዊ ሥርዓት ከፈፀሙ በኋላ ሁሉም ጋብቻዎች በተመሳሳይ የሚመዘገቡበትን አስገዳጅ የምዝገባ ሥርዓት በመዘርጋት የጋብቻ መኖርና አለመኖርን በሚመለከት የሚፈጠሩ ችግሮችን ማስወገድ ይቻላል፣ ይህ ዓይነቱ አስገዳጅ የምዝገባ ሥርዓት እንደሚኖር በዚህ የቤተሰብ ሕግ ውስጥ መደንገግ አለበት የሚል ነው፡፡

በመጨረሻ በማሻሻያው የተወሰደው አቋም ጋብቻ በብሔራዊ የጋብቻ አፈጻጸም ሥርዓት፣ በሀይማኖት ሥርዓትና በባሕላዊ ሥርዓት ሊፈጸም እንደሚችል የሚፈቅድ ነው፡፡ ሆኖም በየትኛውም ዓይነት ሥርአት ቢፈጸም ለጋብቻ አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎች በሙሉ (ዕድሜ፣ ፈቃደኝነት፣ የሥጋና የጋብቻ ዝምድና አለመኖር ወዘተ) መሟላት እንዳለባቸውና ጋብቻውም መመዝገብ እንዳለበት በመደንገግ ነው፡፡ ይህም በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 28 እና 40 ላይ በግልጽ ተደንግጓል፡፡

### 2.3 መተጫጨት

መተጫጨትና ከመተጫጨቱ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች በነባሩ የፍትሐብሔር ሕግ ከቁጥር 560-576 በተፃፉ ድንጋጌዎች ተካተው የሚገኙ ሲሆን በሕጉ በቁጥር 560/1/ ላይ እንደተገለፀው፤

> "መተጫጨት ማለት የእጮኛውና የእጮኛይቱ ቤተ ዘመዶች በልጆቻቸው መካከል ጋብቻ ይኖራል ብለው የነዚሁ የሁለቱ ቤተዘመድ አባሎች የሚያደርጉት ውል ነው፡፡"

መተጫጨት በነባሩ ልማድና የኀብረተሰቡ ባሕል መሠረት ወላጆች የልጆቻቸውን የወደፊት ሕይወትና ኑሮ እነሱ ይጠቅማል በሚሉት መንገድ ለማስኬድ የሚጠቀሙበት ሥርዓት እንደሆነ ተደርጐ ይታያል፡፡ በአገሪቱ በሙሉ አፈፃፀሙ ተመሳሳይ ነው ባይባልም በተለይ ደግሞ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ወላጆች አካለ መጠን ባልደረሱ ልጆቻቸው ላይ ያላቸው ሥልጣን መገለጫ እንደሆነም ይታወቃል፡፡ የቤተሰብ ሕጉን ለማሻሻል ዝግጅት ሲደረግና የነባሩ ሕግ ድንጋጌዎች ሲመረመሩ አንዱ የተነሳው የመተጫጨት ጉዳይ ነበር፡፡ በፍትሕ ሚኒስቴር በተዘጋጀውና በፍትሕና የሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት አማካኝነት ለሕዝብ ለውይይት በተሰራጨው ረቂቅ የቤተሰብ ሕግ ላይ "መተጫጨት ማለት እጮኛውና እጮኛይቱ በመካከላቸው ለወደፊት ጋብቻ ይኖራል ብለው ለወደፊት ጋብቻ ለመፈፀም የሚያደርጉት ስምምነት" እንደሆነ ተሻሽሎ ቀርቦ የነበረ ሲሆን መተጫጨቱ የሚደረገው በወደፊት ተጋቢዎች ቤተዘመዶች መካከል ነው የሚለውን የፍትሐብሔር ሕጉን ድንጋጌ መለወጥ ያስፈለገበት ምክንያት በቤተዘመዶች መካከል መተጫጨት እንዲፈጸም ማድረግ ጊዜው ያለፈበት አስተሳሰብ ከመሆኑም በላይ ጋብቻ በተጋቢዎች ነፃና ሙሉ ፈቃድ ላይ ብቻ ይመሠረታል ከሚለው ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ መንፈስ ጋር አይጣጣምም በሚል እንደሆነ በወቅቱ የተዘጋጀው የረቂቁ ማብራሪያ ወይም ሃተታ በምክንያት ይገልጻል፡፡

ረቂቁ ለውይይት በቀረበበት ወቅት የተለያዩ አከራካሪ ጥያቄዎች ተነስተዋል፡፡ መተጫጨትን በተመለከተ የተነሳው ዋነኛ አከራካሪ ጉዳይ መተጫጨት እስካሁን እንደነበረው በሚሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ውስጥ ዕውቅና አግኝቶ በተቋምነት መቀጠል ይኖርበታል ወይስ አስፈላጊ ስላልሆነ ይሰረዝ የሚለው ሲሆን፤ እንዲቀጥል ከመደረጉ ወይም ካለመደረጉ ጋር ተያይዞ ዝርዝር ጥያቄዎችም ተነስተው ነበር፡፡ በአንድ ወገን የነበረው አመለካከት እስካሁን በሚሠራበት የቤተሰብ ሕግ ውስጥ መተጫጨትን በተመለከተ የተፃፉት ድንጋጌዎች ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ድንጋጌዎች ጋር የማይጣጣሙና የመተጫጨቱ መሠረተ ሓሳብ ዘመናዊነትን ያልተከተለ ስለሆነ መሠረዝ አለበት የሚል ነው፡፡ ለዚህ የቀረበው ምክንያት አሁን ባለው ሕግ የመተጫጨት ውል የሚመሠረተው በወደፊት ተጋቢዎች ወላጆች ወይም ቤተዘመድ ፈቃድ ላይ መሆኑና ከወላጆች ተጽዕኖ ውጭ የተደረገ ነው ማለት አያስደፍርም፡፡ ይህም በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 34/2/ ጋብቻ በተጋቢዎች ነፃና ሙሉ ፈቃድ ላይ ብቻ ይመሠረታል የሚለውን ድንጋጌ የሚፃረር ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል አንዲት ሴትና አንድ ወንድ ለወደፊት ለመጋባት የመተጫጨት ስምምነት ካደረጉ በኋላ አንደኛው ወገን ጋብቻውን ለመፈፀም ፈቃደኛ ካልሆነ ተገዶ እንዲያገባ አይደረግም፡፡ በዚህም ምክንያት መተጫጨት በተቋምነት መቀጠሉ ብዙም ጥቅም ስለሌለው ቢቀር ይሻላል የሚል ነው፡፡

ሁለተኛው አመለካከት ደግሞ መተጫጨት እስካሁን ድረስ ሲሠራበት ብዙ ችግር አልታየበትም፣ ከባህልም አንጻር ሕብረተሰቡ ተቀብሎት እየተጠቀመበት የቆየ በመሆኑ እንደባህላዊ ቅርስ የሚታይ እንጂ አስፈላጊ አይደለም ተብሎ በቀላሉ የሚጣል መሆን የለበትም፣ የወደፊት ተጋቢዎች የመተጫጨት ስምምነት በማድረግ ወደፊት ለሚመሠርቱት ቤተሰብ መሠረት የሚሆን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶችን የሚመሠርቱበት በጐ ተቋም በመሆኑ መተጫጨት በሕግ እውቅና ሊኖረው አይገባም ማለት ይህን ግንኙነት መካድ ይሆናል፣ በተጨማሪም ጋብቻ ለመመሥረት ሁኔታዎችን አሟልተው በአንዳንድ ኢኮኖሚያዊና ግላዊ ችግሮች የሚዘገዩትን ሰዎች ያለምንም ሕጋዊ ሁኔታ እንዲቆዩ ማድረግ ግንኙነታቸውን ማላላት ስለሚሆን የመተጫጨት ስምምነቱ በመካከላቸው መኖር አስፈላጊ ነው፣ ስለዚህ መተጫጨት ለወደፊት ተጋቢዎች ነፃ በሆነ መንገድ የሚደረግ ስምምነት ሆኖ ከሕገ መንግሥቱ በተጣጣመ ሁኔታ ተስተካክሎ መቀጠል ይኖርበታል የሚል ክርክር ነበር፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዘው የተነሱት ጥያቄዎች ደግሞ መተጫጨት በተቋምነቱ በሚሻሻለው ሕግ ዕውቅና አግኝቶ ይቀጥል ከተባለ፣

ሀ. ወላጆች ወይም ቤተዘመድ በመተጫጨቱ ተግባር ሚና ሊኖራቸው ይገባል ወይ?

ለ. የመተጫጨቱ ስምምነት በማናቸውም ምክንያት ሊፈርስ ይችላል ወይስ የማፍረሻ ምክንያቶች ተዘርዝረው በሕጉ ሊገለጹ ይገባል?

ሐ. መተጫጨት በሚፈርስበት ጊዜ ስምምነቱን ያፈረሰው ወገን ካሳ መክፈል አለበት? ካሳ የሚከፈል ከሆነ መጠኑን ለመወሰን ምን መመዘኛዎችን መጠቀም ያስፈልጋል?

መ. ወንዱና ሴቲቱ በመተጫጨት ስምምነት ውስጥ እያሉ ያፈሩት የጋራ ሀብት ቢኖር፣ አንዱ ለሌላው የሰጠው ስጦታ ቢኖር፣ የሀብቱ ክፍፍል እንዴት ይታያል? ስጦታውስ መመለስ አለበት ወይ?

ሠ. የጋብቻ ዕድሜ ከመድረሱ በፊት የመተጫጨት ስምምነት ማድረግ ሕጋዊ ተቀባይነት ሊኖረው ይችላል ወይ? የሚሉት ናቸው፡፡

እነዚህን ጥያቄዎች በሚመለከት በየአውደ ጥናቶች በተካሄዱ ውይይቶች የተለያዩ አስተያየቶች ተሰንዝረዋል፡፡ የመጀመሪያውን በተመለከተ መተጫጨቱ በዋናነት በወደፊት ተጋቢዎች ፈቃድ ላይ ብቻ የተመሠረተ መሆን አለበት የሚል አመለካከት ሲኖር በሌላ በኩልም ወላጆችና ቤተዘመዶች በመተጫጨቱ ላይ ያላቸው አስተያየት መጠየቅ አለበት የሚል አስተሳሰብ የነበራቸው ወገኖች ነበሩ፡፡

ሁለተኛውን ጥያቄ በተመለከተ ደግሞ ጋብቻ ያለተጋቢዎች ፈቃድ ሊደረግ የማይችል በመሆኑ መተጫጨት በማናቸውም ምክንያት ፈራሽ ሊሆን እንደሚችል በሕጉ መደንገግ አለበት የሚል አመለካከት የነበረ ሲሆን በሌላው ወገን ደግሞ መተጫጨቱ ሊፈርስ የሚችልባቸው ምክንያቶች ተዘርዝረው ቢቀመጡ ጥሩ ይሆናል የሚል አስተሳሰብ እንዳለ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በሦስተኛ ደረጃ የተነሳው መተጫጨት ሲፈርስ ያፈረሰው ወገን ካሳ መክፈል አለበት ወይ የሚለው ነው፡፡ ይህን በተመለከተ የነበረው አስተያየት በአብዛኛው ተመሳሳይ ነው፡፡ ይኸውም አንድ ሰው ወደፊት ለመጋባት የመተጫጨት ስምምነት ካደረገ በኋላ ያለበቂ ምክንያት ስምምነቱን ካፈረሰ ለመተጫጨቱ የተደረገውን ወጭና ጋብቻው ይፈፀማል በሚል ለተደረጉ ዝግጅቶች የወጣን ወጭ መክፈል እንዳለበትና በተጨማሪም የመተጫጨቱ መፍረስ ለሚያስከትለው የሕሊና ጉዳት ለመፍረሱ ምክንያት ላልሆነው ወገን ካሳ ሊከፈለው እንደሚገባ፣ የካሳው መጠንም በመወያያ ረቂቅ ሕጉ ላይ በተገለፀው መሠረት ከአስር ሺህ ብር የማይበልጥ ሆኖ በርትዕ በዳኞች ሊወሰን እንደሚገባው የብዙዎች እምነት ነበር፡፡

ሌላው አከራካሪ ጉዳይ የመተጫጨትን ስምምነት ከጋብቻ ዕድሜ ጋር በማያያዝ የተነሳው ጥያቄ ነው፡፡ ይህን በሚመለከት በየአውደ ጥናቶቹ በጉዳዩ ላይ በተደረገው ውይይት ሁለት ዓይነት አቋሞች ተንፀባርቀዋል፡፡ በአንድ በኩል ያለው አመለካከት የመተጫጨት ስምምነት ወደፊት ለመጋባት የሚደረግ ስምምነት በመሆኑ የጋብቻ ዕድሜ ሳይደርስም ቢሆን ተጫጭቶ የተወሰነ ጊዜ መቆየት የማይቻልበት ምክንያት አይኖርም በማለት በአንዳንድ ክልሎች በተለይም በገጠር አካባቢዎች የነበረውን ወላጆች ሕጻናት ልጆቻቸውን አስመልክቶ ያደርጉት የነበረውን የቆየ ልማድ ያንጻባረቀ ክርክር ቀርቦ የነበረ ሲሆን በሌላ ወገን ያለው አመለካከት ደግሞ የመተጫጨት ስምምነት ወደፊት በጋብቻ ለመተሳሰር እስከሆነ ድረስ በቀላሉ ሊታይ የሚገባው

አይደለም፣ መተጫጨት በነፃ ፈቃድና ፍላጐት ላይ የተመሠረተ እስከሆነ ድረስ አንድ ሰው የጋብቻ ዕድሜው ከመድረሱ በፊት የመተጫጨት ስምምነት ቢያደርግ ዋጋ የሌለው ስለሚሆን የጋብቻ እድሜ ከደረሰ በኂላ ወዶና ፈቅዶ ሊያደርገው ስለሚገባ ከጋብቻ እድሜ በፊት የመተጫጨት ስምምነት ማድረግ በሕጉ መፈቀድ የለበትም የሚል ነው፡፡

በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ የመጀመሪያ ረቂቅ ከአንቀጽ 8 እስከ 17 ስለመተጫጨት ተደንግጎ የነበረ ቢሆንም፣ መተጫጨትና የሚኖረው ሕጋዊ ውጤት በርካታ ጥያቄዎችን በማስነሳት ብዙ ካከራከረ በኂላ በመጨረሻ ሙሉ በሙሉ ከሕጉ እንዲሰረዝ ተደርጓል፡፡ የመተጫጨት ስምምነት ከሕጉ ተሰርዞዘ ማለት ግን ለጋብቻ ዕድሜ የደረሱ የወደፊት ተጋቢዎች ይህን መሰል ስምምነት እንዳያደርጉ በሕግ ተከልክሏል ማለት አይደለም፡፡ ስለሆነም ሕጉ ኅብረተሰቡ እንደ ባህሉና አካባቢያዊ ልማዱ ሁለት የወደፊት ተጋቢዎች ተጫጭተው መቆየታቸውን አይከለክልም፡፡ በተግባር ሲፈፀምም ይታያል፡፡ እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ የመተጫጨት ስምምነት መኖርም ሆነ የስምምነቱ መፍረስ ምን ሕጋዊ ውጤት ሊያስከትል ይችላል የሚለው ነው፡፡ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ መሠረት ምንም የሚያስከትለው ሕጋዊ ውጤት አይኖርም፡፡ ይህ የፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግ ከወጣ በኂላ ብዙ ክልሎች የራሳቸውን የቤተሰብ ሕግ አውጥተዋል፡፡ ከነዚህ አንዱ የአማራ ብሔራዊ ክልል ሲሆን በ1995 በወጣው የክልሉ የቤተሰብ ሕግ መሠረት አካለ መጠን በደረሱ አንድ ወንድና አንዲት ሴት መካከል ለወደፊት ትዳር ለመመሥረት የመተጫጨት ውል ሊያደርጉ እንደሚችሉና ውሉም ሕጋዊ ውጤት እንደሚኖረው ተደንግጓል፡፡

ከላይ ከተመለከቱት ጉዳዮች በተጨማሪ ለጋብቻ ክልከላ የሚያበቁ ሁኔታዎችን፣ ከትዳር ውጭ እንደባልና ሚስት መኖርን፣ የቤተዘመድ ሽምግልና ጉባኤን፣ ፍቺን፣ ፍቺ የሚያስከትላቸውን ውጤቶች፣ ወዘተ… በሚመለከት ከዚህ በታች የተገለፁት አከራካሪ ነጥቦች ተነስተዋል፡፡

## 3. በኅብረተሰቡ ስለጋብቻ ክልከላ (Impediments to marriage) ማሻሻያ ድንጋጌዎች የተነሱ ዋና ዋና አከራካሪ ጉዳዮች

በፍትሐብሔር ሕጉ ተካቶ ሲሠራበት በኖረው የቤተሰብ ሕግ ጋብቻ ከሦስቱ የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓቶች በየትኛውም ሥርዓት ይፈፀም ጋብቻው ከመፈፀሙ በፊት መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች ወይም የጋብቻ ሁኔታዎች አሉ፡፡ እነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች ከዝምድና ሁኔታ፣ ከዕድሜ፣ አስቀድሞ ሌላ ጋብቻ ከመኖርና አለመኖር፣ የተጋቢዎች ነፃ ፈቃድ ከመኖርና አንዲት ሴት የመጀመሪያ ጋብቻዋ ከፈረሰ በኂላ ለማግባት መቆየት ካለባት የተወሰነ የጊዜ ገደብ ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ የቤተሰብ ሕጉን በማሻሻሉ ሂደት በነበረው የሕዝብ ተሳትፎ በተለይም ዝቅተኛውን የጋብቻ ዕድሜ ከመወሰን፣ ጋብቻን ከሚከለክለው የሥጋ ዝምድና ደረጃና ከአንድ በላይ ጋብቻን ከመፍቀድ ወይም ከመከልከል ጋር በተያያዘ የኅብረተሰቡ አመለካት በሰፊው የተለያየና የተለያዩ ጥያቄዎችን ያስነሳና ብዙ ክርክር የታየበት ነበር፡፡

### 3.1 የጋብቻ ዕድሜ

በሕግ ፊት የሚጸና ጋብቻ ለመፈጸም መሟላት ካለባቸው አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎች አንዱና በማሻሻያው ሂደት አከራካሪ የነበረው ጉዳይ የጋብቻ ዕድሜን አስመልክቶ የተነሳው ጥያቄ ነው፡፡ በነባሩ የፍትሐብሔር ሕግ ዝቅተኛው የጋብቻ ዕድሜ የወንድ 18 ዓመት የሴት 15 ዓመት ነበር፡፡ ይህ ልዩነት እንዳለ መቀጠል አለበት ወይስ የሴት ዝቅተኛው የጋብቻ ዕድሜ ከወንዶች እኩል 18 ዓመት መሆን አለበት በሚለው ጥያቄ ላይ በኅብረተሰቡ ዘንድ አንድ ዓይነት አመለካከት አልነበረም፡፡ በጉዳዩ ላይ በተደረገው ውይይት አንድ ሰው አካለ መጠን ደረሰ የሚባለው 18 ዓመት ሲሞላው መሆኑ በሕግ ተደንግጐ እያለ ይህ ዕድሜ ከመሙላቱ በፊት አንዲት ሴት ጋብቻ እንድትፈጽም ማድረግ ጋብቻውን አውቃና ፈቅዳ አድርጋለች ለማለት የማያስችል ከመሆኑም በላይ በወንድና በሴት መካከል ልዩነትን የሚፈጥር አድሏዊ ስለሆነ የጋብቻ ዕድሜ ለወንድም ለሴትም እኩል 18 ዓመት መሆን አለበት የሚለው የብዙዎች አመለካከት ነበር፡፡ የዚህ አመለካከት አራማጆች ያነሷቸው ፖሊሲ ነክ የሆኑ ሌሎች ማሳመኛ ነጥቦች ነበሩ፡፡ ከነዚህም መካከል የብሔራዊ የሥነ ሕዝብ ፖሊሲና የትምህርት ፖሊሲዎች

ይጠቀሳሉ፡፡ በ1989 ዓ.ም. በወጣው ብሔራዊ የሥነ ሕዝብ ፖሊሲ እንደተገለፀው የወሊድ ምጣኔን ለመቀነስ የሴት ልጅን የጋብቻ እድሜ በሕግ ከፍ አድርጐ መደንገግ ያስፈልጋል፣ የቤተሰብ ሕግ የሥነ ሕዝብ ፖሊሲውን ከማስፈፀም አንፃር ጭምር መታየት እንዳለበትና በተጨማሪም የጋብቻ ዕድሜ ከፍ ብሎ በሕግ መደንገጉ የሴት ልጆችን የትምህርት ተሳትፎ በማሳደግ የትምህርት ፖሊሲውንም ለማሳካት ያግዛል የሚሉ ነበሩ፡፡

በሌላው ወገን የነበረው አስተሳሰብ ደግሞ ለጋብቻ ብቁ የሚያደርገውን የዕድሜ መጠን መወሰን የአካል ብቃትን፣ የአዕምሮ ብስለትን፣ የኑሮና የጤንነት ሁኔታን፣ ባህላዊና ዘመናዊ አስተሳሰቦችን ማገናዘብን እንደሚጠይቅና በአሁኑ ጊዜ በአገራችን አብዛኛው ሕዝብ የገጠር ነዋሪ በመሆኑ የትምህርት ዕድልም ስላልተስፋፋ ሴት ልጆች 18 ዓመት እስከሚሞላቸው ባል ሳያገቡ እደሚቆዩ በሕግ መከልከል በተጨባጭ ችግር ሊያስከትል የሚችልና ሕጉን ለማስፈጸምም አስቸጋሪ ስለሚሆን በሕግ ከመከልከል ይልቅ ሕዝቡን ማስተማር እንደሚሻልና በነባሩ ሕግ የተደነገገው የ15 ዓመት የዕድሜ ገደብ ቢቀጥል እንደሚሻል የተደረጉ ክርክሮች ነበሩ፡፡ በመጨረሻ የቀረበው ረቂቅ ዝቅተኛ የጋብቻ እድሜን ለወንድም ለሴትም እኩል 18 ዓመት ያደረገ ሲሆን በሕግ አውጭው አካልም የፀደቀው ይኸው ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለፀው የዚህ ሕግ ተፈጻሚነት በፌዴራል መንግሥት ሥር ባሉት አዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተሞች ላይ በመሆኑ አንዳንድ ክልሎች ባወጡት ክላላዊ የቤተሰብ ሕግ ለምሳሌ በትግራይ ክልል ዝቅተኛው የጋብቻ ዕድሜ ለወንድም ለሴትም ዕኩል ሀያ አንድ ዓመት እንዲሆን ተደርጓል፡፡

### 3.2 የሥጋ ዝምድና

ሌላው አወዛጋቢ ጥያቄ ጋብቻን የሚከለክለው የሥጋ ዝምድና ደረጃ ስንት መሆን አለበት የሚለው ነበር፡፡ በነባሩ የፍትሐብሔር ሕግ መሠረት የሥጋ ዝምድና ደረጃ እስከ ሰባት ትውልድ የሚዘልቅ ነው፡፡ አቆጣጠሩም የጋራ ከሆነው የግንድ ወላጅ ጀምሮ ግራና ቀኝ ካለው ትውልድ መስመር እስከ ሰባት ትውልድ ድረስ እንደሆነ በፍትሐብሔር ሕግ በቁጥር 551/2/ ላይ ተመልክቷል፡፡ በዚህ የዝምድና ደረጃ ውስጥ በሚገኙ ሰዎች መካከል ጋብቻ ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡ ጋብቻ ተፈጽሞ ከተገኘም እንዲፈርስ የሚደረግ ሲሆን የወንጀል ቅጣትም ያስከትላል፡፡ በዚህ ሁኔታ ላይ የተነሳው ጥያቄ በአንድ በኩል ጋብቻን የሚከለክለው የዝምድና ደረጃ የተንዛዛ ስለሆነ ዝቅ ማለት እንዳለበትና በአንዳንድ ማኅበረሰቦች ዘንድም ከሰባት ትውልድ በታች ባለ የዝምድና ደረጃ ያሉ ሰዎች ጋብቻ የሚፈጽሙበት ሁኔታ በተግባር ስላለ የዝምድና ደረጃን ዝቅ ማድረግ እውነታውን መቀበል ነው የሚል ክርክር ቀርቧል፡፡ ለሕዝብ ውይይት ተዘጋጅቶ የቀረበው ረቂቅም ይህን አስተሳሰብ በመከተል ይመስላል የዝምድና ደረጃውን ከሰባት ወደ አምስት ትውልድ ዝቅ በማድረግ የቀረበ ነበር፡፡[6]

በሌላ በኩል ግን የዝምድና ደረጃ ከሰባት ትውልድ ወደ አምስት ዝቅ የሚልበት አሳማኝ ምክንያት ባለመኖሩና በዘመዳሞች መካከል ጋብቻ ማድረግን የሚያበረታታ ስለሚሆን፣ በሕክምና ሳይንስ ረገድም በዘር የሚተላለፉ በሽታዎችን ከመቆጣጠር አንፃር ጠቀሜታው ከፍተኛ ስለሆነ ሕጉ ባለበት እንዲቀጥልና ከሰባት ትውልድ በታች ጋብቻ መፈቀድ የለበትም የሚል ጠንካራ ተቃውሞ ነበር፡፡ ይህም በተለይ በውይይቱ ተሳታፊ በነበሩ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ተወካዮች በኩል ትኩረት የተደረገበት ጉዳይ ነበር፡፡ እንደሕክምና ሳይንስ አዋቂዎች ከሆነ በዘመዳሞች መካከል የሚፈፀም ጋብቻ በዘር የሚተላለፉ በሽታዎችን ሕክምና አስቸጋሪና ውስብስብ የማድረግ ዕድሉ የሰፋ ነው፡፡ ስለዚህ ክልከላው ከሀይማኖት፣ ከባሕልና ልምድ አንፃርም ብቻ ሳይሆን በሽታን በመከላከል አንፃርም ሊታይ እንደሚገባ የሚያሳስቡ ክርክሮች ተደምጠዋል፡፡ በመጨረሻም ለሕግ አውጭው አካል ቀርቦ የፀደቀውና ሕግ ሆኖ የወጣው ረቂቅ የተከተለው አካሄድ ግን የተለየ ነው፡፡ የተሻሻለው ሕግ የተከተለው የክልከላ አካሄድ የትውልድ ደረጃን በመቁጠር ሳይሆን ጋብቻ በቀጥታ ዘመዳሞች (በወላጆችና በተወላጆች) መካከል ወደጎን በሚቆጠር ዝምድና ደግሞ ከእህት፣ ከአክስት፣ ከወንድምና ከአጐት

---

[6] የተሸሻለው የቤተሰብ ሕግ የመጀመሪያ ረቂቅ አንቀጽ 2

ጋር መፈጸም እንደማይቻል በመደንገግ ብቻ የሚያበቃ ነው፡፡ ከዚህ በሰፋ ደረጃ ክልከላውን መቀጠል የሚፈልጉ የኅብረተሰብ ክፍሎች ቢኖሩ እንደሀይማኖታቸውና ባህላቸው መቀጠል የሚችሉ ሲሆን ሀይማኖታዊና ባህላዊ ልምድን ብቻ መሠረት በማድረግ የተደረገ ክልከላ ተጥሶ ቢገኝ ግን የሚያስከትለው ሕጋዊ ውጤት አይኖርም፡፡[7]

### 3.3 ከአንድ በላይ ጋብቻን መፍቀድ ወይም መከልከልን በተመለከተ

የቤተሰብ ሕጉን በማሻሻሉ ሂደት ሰፊ ክርክር አስነስቶ የነበረው ሌላ ጉዳይ ከአንድ በላይ ጋብቻ መፈፀም ወይም አንድ ወንድ ከአንድ በላይ ሴት ማግባት ክልከላ ሊደረግበት ይገባል ወይ የሚለው ነው፡፡ በጉዳዩ ላይ በተለያዩ አውደጥናቶችና ኮንፍረንሶች ታሳታፊ የነበሩ የልዩ ልዩ ሀይማኖቶች መሪዎችና ተከታዮቻቸው፣ ምሁራን፣ የሴቶች ማህበራትና ሌሎችም ሲቪል ማህበራት የተለያዩ አቋሞችን ይዘው በሰፊው ተከራክረዋል፡፡ ክርክሮቹ ሀይማኖታዊ፣ ባህላዊና ሕጋዊ ይዘት ያላቸው እንደነበሩ ከሚቀርቡት ሀሳቦች መገንዘብ ይቻላል፡፡ በኦርቶዶክስ ክርስትና ሀይማኖት መሪዎችና ተከታዮቻቸው ዘንድ የነበረው አመለካከት ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ ከአንድ በላይ ጋብቻ ከሀይማኖቱ ቀኖና ውጭ የሆነና በተጋቢዎች መካከልም መተማመንን የሚያዳክም፣ ለቤተሰብ ጥንካሬና ፍቅርም የማይበጅ ስለሆነ በሕግ መከልከሉ አግባብ ነው የሚል ሲሆን የእስልምና ሀይማኖት ተከታዮች በበኩላቸው በሕገ መንግሥቱ የተረጋገጠውን የሀይማኖትና የእምነት ነፃነት የሚጋፋና ጋብቻን በተመለከተ ከአንድ በላይ ጋብቻ ለማድረግ የሚያስፈልገውን ሥርዓት እስከተከተሉ ድረስ ነገሩ የሀይማኖት ጉዳይ እንጂ መንግሥት በሕግ ሊከለክል የሚገባው አይደለም የሚል ነበር፡፡ በእስልምና ሀይማኖት ተከታይ ወገኖች ዘንድ በጉዳዩ ላይ ይነሱ የነበሩ ክርክሮች በአብዛኛው በ1987 ዓ.ም. የፌዴራሉን ሕገ መንግሥት ለማጽደቅ በተደረጉ ውይይቶች ይነሱ ከነበሩ ክርክሮች ጋር ተመሳሳይ ነበሩ፡፡

በሴቶች ማህበራትና በሌሎች ከሴቶች መብቶች ጋር በተያያዘ የሚሰሩ የሲቪል ማህበራት ያነሷቸው የነበሩ ክርክሮች ሕገመንግሥቱን መሠረት በማድረግ ይነሱ የነበሩ ናቸው፡፡ በነዚህ ወገኖች እምነት ከአንድ በላይ ጋብቻ እንዲፈቀድ የሚቀርቡ አስተያየቶች ሀይማኖታዊም ይሁን ባህላዊ ይዘት ይኑራቸው ከሕገመንግሥቱ ጋር የሚጣጣሙ አይደሉም፡፡ በተለይም ሴቶች በሚገኙበት የኢኮኖሚ የበታችነትና የባህል ተጽዕኖ ምክንያት የሴቷ ነፃና እውነተኛ ፈቃድ ይኖራል ማለት እንደማይቻል ተከራክረዋል፡፡ ስለዚህ በጋብቻ ላይ ጋብቻ እንዲፈፀም በቤተሰብ ሕጉ ላይ መፍቀድ ጋብቻ በተጋቢዎች ሙሉ ፈቃድ ላይ እንዲመሠረትና አንድ ወንድና አንዲት ሴት በጋብቻ አፈፃፀም፣ በጋብቻው ዘመንና በፍች ጊዜም እኩል መብት እንዳላቸው በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 34 የተደነገገውን የሚቃረን ነው፡፡ ስለዚህ ጠንካራ መሠረት ያለው ቤተሰብ ለመገንባት፣ ልጆችን በአግባቡ ለማሳደግና የሴቶችን መብትም ለማስከበር በጋብቻ ላይ ሌላ ጋብቻ እንዳይፈፀም በሕግ መከልከሉ ተገቢና ሕገመንግሥታዊ መሠረት ያለው ነው የሚለው ክርክር በየመድረኮቹ ሲስተጋባ ቆይቷል፡፡ በጋብቻ ላይ ጋብቻ እንዲፈቀድ ይደግፉ የነበሩ ወገኖች ጉዳዩን ከሃይማኖት አንፃር ብቻ በማየት ሳይሆን ባህልንና ልማድን መሠረት ያደረገ ክርክርም ሲያቀርቡ ታይቷል፡፡ አንዳንዶቹ ከአንድ በላይ ጋብቻ መኖሩ ብዙ ልጅ ለመውለድ እንደሚያስችልና የልጅ መብዛት ደግሞ ሀብት በመሆኑ የሚደገፍ እንጂ የሚነቀፍ መሆን እንደሌለበት ሲከራከሩ ታይቷል፡፡

በመጨረሻ በተሻሻለው ሕግ የተወሰደው አቋም በጋብቻ ላይ ጋብቻን የሚከለክል ነው፡፡ በዚህም መሠረት ሕገመንግሥቱ ባልና ሚስት በጋብቻው እኩል መብት ያላቸው መሆኑን በግልጽ ስለሚደነግግ በጋብቻ ውስጥ እስካሁን ድረስ ሚስት ሌላ ባል ማግባት እንደማትችል ሁሉ ባልም ሌላ ሚስት ሊኖረው አይገባም በሚል አስተሳሰብ ማንኛውም ሰው አስቀድሞ በጋብቻ የተሳሰረ ከሆነ ይኸው ጋብቻው ፀንቶ ባለበት ጊዜ ሌላ ጋብቻ መፈፀም አይችልም በሚል ደንግጓል፡፡

---

[7] በ1996 በወጣው የወንጀል ሕግ በሥጋ ዘመዶች መካከል ጋብቻ ማድረግ የሚያስቀጣ ድርጊት ነው፡፡

## 4. ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት አብሮ መኖርን በሚመለከት (Irregular Union)

ጋብቻ በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል በነፃና ሙሉ ፈቃደኝነት ላይ ተመሥርቶና አስፈላጊ የጋብቻ ሁኔታዎችን አሟልቶ የሚፈፀም እንደሆነ በሕጉ ተገልጿል። ይሁን እንጂ አንድ ወንድና አንዲት ሴት ሕጋዊውን ሥርዓት ተከትለው በባልና ሚስትነት ሳይጋቡ አብረው የሚኖሩበት ሁኔታ እንዳለ በተግባር ይታወቃል። ይህ ሁኔታ በነባሩ የፍትሐብሔር ሕግ ከጋብቻ ውጭ በግብረ ሥጋ ግንኙነት አብሮ መኖር (Irregular Union) በመባል ይታወቃል።

የቤተሰብ ሕጉን በማሻሻሉ ሂደት ይህን ጉዳይ በተመለከተ በተለያዩ ዐውደ ጥናቶች በተደረጉ ውይይቶች በርካታ ጥያቄዎች የተነሱ ሲሆን የተለያዩ አመለካከቶችም ተንፀባርቀዋል። የተነሱት ጥያቄዎች ጠቅለል ባለ ሁኔታ ሲታዩ ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር አዲስ በሚሻሻለው ሕግ ዕውቅና አግኝቶ እንደተቋም መቀጠል አለበት ወይ? ይቀጥል ከተባለስ የሚያስከትላቸው ውጤቶች ምን ሊሆኑ ይገባል? እንደዚህ ዓይነቱን ግንኙነት ዕውቅና ሰጥቶ እንዲቀጥል ማድረግስ ከሕገ መንግሥቱ አንፃር እንዴት ይታያል? ሕጋዊ ጋብቻን አያዳክምም ወይ? በሕግ እውቅና እንዳይኖረው ማድረጉስ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ መካድና በማወቅም ይሁን ባለማወቅ በግንኙነት ውስጥ ያሉ ሰዎችን መብት በተለይ የሴቷን የሚጐዳ አይሆንም ወይ? የሚሉ ነበሩ።

በመጀመሪያ በፍትሕ ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ በፍትሕና ሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት ለውይይት በቀረበው ረቂቅ "ከጋብቻ ውጭ በግብረ ሥጋ ግንኙነት አብሮ መኖር" በመባል የሚታወቀው ግንኙነት ከረቂቅ ሕጉ እንዲሰረዝ ተደርጐ ነበር። ለመሰረዙ የተሰጠው ምክንያትም ግንኙነት በሕገመንግሥቱ በባህልም ሆነ በሀይማኖት ድጋፍ የሌለው፣ ከኅብረተሰቡ መደበኛ አኗኗር ያፈነገጠ፣ ወንዱንና ሴቷን በእኩል የማያይና በተግባር ችግር ያስከተለ ስለሆነ በመጋባትና ባለመጋባት መካከል ሕጋዊና እውቅና ያለው ሌላ ግንኙነት መፍጠር አስፈላጊ አይደለም የሚል ነበር።

እነዚህን ጥያቄዎች መሠረት አድርገው በተካሄዱ ሰፊ ውይይቶች ግንኙነቱ በሚሻሻለው የቤተሰብ ሕግ እውቅና አግኝቶ መቀጠል አለበት እና በሕጉ ውስጥ ሊካተት አይገባውም የሚሉ ሁለት ተፃራሪ አመለካከቶች ነበሩ። ሁለቱንም አስተሳሰቦች የሚያራምዱ ወገኖች የሚያቀርቧቸው የየራሳቸውን ምክንያቶች ነበሯቸው። ግንኙነቱ ሕጋዊ እውቅና አግኝቶ በሚሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ሊቀጥል ይገባል የሚሉ ወገኖች ያቀርቧቸው የነበሩ ምክንያቶች:-

ሀ) በሕገ መንግሥቱ እንዲህ ዓይነት ግንኙነት በሕግ እውቅና እንዳይሰጠው በግልጽ ያልተከለከለ በመሆኑ መፈቀድ ይኖርበታል፤

ለ) ጉዳዩ በተግባር የኖረና አሁንም ያለ በተለይም በከተሞች አካባቢ ከዘመናዊ ኑሮ ጋር ተያይዞ ይበልጥ እየተለመደ የመጣ በመሆኑ፣ ዕውቅና መንፈግ ማለት ነባራዊውን ሁኔታ መካድ ከመሆኑም በላይ በተግባር መከልከል አይቻልም፤

ሐ) ይህን መሰሉ ግንኙነት ሕጋዊ ዕውቅና እንዳይኖረው ማድረግ በተለይም ሳያውቁ በተለያየ የኢኮኖሚ ችግር ምክንያት ወደ ግንኙነቱ የሚሳቡት ሴቶች መብት የሚጐዳ ስለሚሆን የነዚህን ሴቶች መብት ለመጠበቅ ግንኙነቱ እውቅና ኖሮት በሚፈርስበት ጊዜም የሴቷን ጥቅም በሚያስጠብቅ መልኩ ተስተካክሎ ከቀድሞ በተሻለ መልኩ ሊቀጥል ይገባዋል፤

መ) የጋብቻ አፈፃፀምም ሆነ የፍቺ ሥርዓት በሕጉ ጠበቅ ያለ በመሆኑ በዚህ ዓይነት ግንኙነት መኖር የቀለለና አቋራጭ መንገድ ስለሆነ ቢፈቀድ ይመረጣል፤

የሚሉ ነበሩ።

ግንኙነቱ በአዲሱ ሕግ እውቅና ሊሰጠው አይገባም በሚለው አመለካከት ይቀርቡ የነበሩት ምክንያቶች ደግሞ:-

ሀ) መንግሥት ሕግ በማውጣትና የተለያዩ ሥርዓቶችን በመቀየስ ጥበቃና እንክብካቤ ሊያደርግ የሚገባው በሕገ መንግሥቱ እንደተገለፀው ለሕጋዊ ጋብቻና ቤተሰብ እንጂ ከሕጋዊ ጋብቻ ውጭ ለሚፈጠር ግንኙነት መሆን የለበትም፤ ስለዚህ በሕገ መንግሥቱ እውቅና ያልተሰጠውን ጉዳይ በቤተሰብ ሕጉ ማካተት ተገቢ አይሆንም፤

ለ) ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር ሕጋዊ ጋብቻን የሚያላላና ትርጉም የለሽ የሚያደርግ ከመሆኑ ባሻገር፣ ግንኙነቱን የመሠረቱት ሰዎችም በቀላሉ የሚያፈርሱት ስለሆነ ለቤተሰብ ብሎም ለኅብረተሰብ የኃላፊነት ስሜት እንዳይኖራቸው ያደርጋል፤

ሐ) አንድ ሰው በተለይ ወንዱ ተመሳሳይ የሆኑ በርካታ ግንኙነቶች እንዲመሠርት ስለሚያደፋፍርና ይህም የሴቶችን መብት በተለያየ ሁኔታ ሊጎዳ ስለሚችል መፈቀድ የለበትም፤

መ) አስተሳሰቡ ኋላ ቀርና የፊውዳሉ ሥርዓት ቅሪት በመሆኑ በሕግ መከልከል ይኖርበታል፤

ሠ) ግንኙነቱ በማናቸውም ጊዜ ስለሚፈርስ ከዚህ መሰል ግንኙነት በሚወለዱ ሕፃናት አስተዳደግ ላይ የሥነ ልቦና ተጽዕኖ የሚያሳድር ከመሆኑም በላይ አወዛጋቢ የአባትነት ጥያቄም ያስነሳል፤

ረ) ግንኙነቱ በባህልም በሀይማኖትም ተደጋፊነት ስለሌለው ሊበረታታና ሕጋዊ እውቅና ሊሰጠው አይገባም፤

ሰ) በአጠቃላይ ይህን መሰሉ ግንኙነት በሕግ እውቅና ኖሮት መቀጠሉ ለኅብረተሰቡ በአጠቃላይና ለሴቶችና ለሕፃናት መብቶች ጉዳት እንጂ ጥቅም የለውም፤

የሚሉ ናቸው።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት እና በሁለቱም ወገን ይቀርቡ የነበሩ ክርክሮችና ምክንያቶቻቸው በርካታ ደጋፊም ተቃዋሚም የነበራቸው ሲሆን ግንኙነቱ ሕጋዊ እውቅና ሊሰጠው አይገባም የሚለው ወገን ያመዝን እንደነበር መገንዘብ ተችሏል። ጉዳዩ ካስነሳው ሰፊ ክርክርና የአመለካከት ልዩነት አንፃር የፖሊሲ ውሳኔ የሚጠይቅ በመሆኑ የመጨረሻው ረቂቅ ለመንግሥት የቀረበው ሁለቱንም አማራጮች በማካተት ነበር። በሚኒስትሮች ምክር ቤት በረቂቁ ላይ በተደረገው ውይይት በመንግሥት የተደገፈው አማራጭ ግንኙነቱ እውቅና እንዲኖረው የሚፈቅደው ሲሆን የተሻሻለው ረቂቅ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ፀድቆ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከቀረበ በኋላ ሕጋዊ ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት የሚኖሩ ጥንዶች ግንኙነታቸው በንብረት ረገድ በሚኖረው ውጤት ላይ መጠነኛ ለውጥ ተደርጉበታል።

በዚህም መሠረት ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ ሰዎች የንብረት አስተዳደራቸውን አስመልክቶ የሚያደርጉት ውል እንደተጠበቀ ሆኖ ከአምስት ዓመት ያላነሰ ጊዜ አብረው ከኖሩ በግንኙነቱ ውስጥ እያሉ ያፈሯቸው ንብረቶች የጋራ ሀብታቸው ይሆናሉ የሚለው አንቀጽ 102/1/ ጊዜው ከአምስት ዓመት ወደ ሦስት ዓመት ዝቅ እንዲል ተደርጓል።[8] የጊዜ ገደብ የማስቀመጡ ጉዳይም በራሱ አከራካሪ ነበር። ምንም እንኳን ሕጉ ሁለቱም ጾታ የሚመለከት ቢሆንም የጊዜ ገደብ መቀረጡን በሚደግፉ ወገኖች እምነት ንብረት ለማበጀት የሚበቃ ነው ተብሎ የሚገመት የጊዜ ገደብ በሕጉ መቆረጡ አብዛኛውን ጊዜ ግንኙነቱ ሲፈርስ በንብረት ክፍፍል ላይ ተጎጅ የሚሆኑት ሴቶች ናቸው ከሚል እምነት በመነጨ ምክንያት የሴቶችን መብት ለማስከበር ይጠቅማል በማለት ነው።

## 5. ስለ ቤተዘመድ ሽምግልና ጉባኤ

በነባሩ የፍትሐብሔር ሕግ መሠረት በባልና ሚስት መካከል የሚነሱ ችግሮችንና አለመግባባቶችን ተመልክቶ የማስታረቅና ሊታረቁ በማይችሉበት ጊዜ ፍችን፣ በፍች ጊዜ የንብረት ክፍፍልን፣ የሕጻናትን አስተዳደግ፣ ቀለብ መስጠትን ወዘተ... ተመልክቶ ውሳኔ የሚሰጥ የቤተዘመድ ሽምግልና ጉባኤ የሚባል ተቋም እንደነበረ ይታወቃል። የዚህን ተቋም ጠንካራና ደካማ ጐኖች በተመለከተ አንዳንድ ውሱን ጥናቶች እንደተደረጉ የሚታወቅ ሲሆን

8 የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ ረቂቁ ቤተሰብ ሕግ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ውይይት ሲደረግበትና እንዲሁም በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሕግ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በአስረጅነት ተገኝቶ ውይይቱን ለመከታተልና ማብራሪያ ለመስጠት ዕድል አግኝቶ ነበር። ጊዜውን ከአምስት ዓመት ወደ ሦስት ዓመት የማሳጠሩ ውሳኔ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተላለፈው ለሴቶች መብት መከበር የሚሠሩ የሲቪል ማህበራትና የፓርላማ የሴቶች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ ባደረጉት ሰፊ ክርክርና ግፊት እንደነበር ፀሐፊው ያስታውሳል።

የተቋሙን አስፈላጊነትና ሚና በሚመለከት የተለያዩ አሉታዊና አዎንታዊ አመለካከቶች እንዳሉ የቤተሰብ ሕጉን በማሻሻሉ ሂደት ታይቷል፡፡

በነባሩ የቤተሰብ ሕግ የነበረውን የቤተዘመድ ሽምግልና ጉባኤን በሚመለከት በዋናነት ሁለት ዓይነት አስተሳሰቦች ነበሩ፡፡ አንደኛው አመለካከት የቤተዘመድ ሽምግልና ጉባኤ በብዙ ችግሮች የተተበተበ፣ በሕጉ የታለመለትን ዓላማ የሳተና በሴቶች ላይ በደልና መጉላላትን ሲያደርስ የኖረ ተቋም በመሆኑ ከአዲሱ የቤተሰብ ሕግ ሙሉ በሙሉ ተሰርዞ በቤተዘመድ ሽምግልና ዳኞች ይከናወኑ የነበሩ ተግባራት በሙሉ ለፍርድ ቤት መሰጠት አለባቸው የሚል ጠንካራ አቋም ነበር፡፡ ለሴቶች መብት መከበር የሚሠሩ ድርጅቶች የሚያነሱት ሌላም መከራከሪያ ነበር፡፡ ይኸውም የቤተዘመድ ሽምግልና ጉባኤ ሕጉ በሥራ ላይ በቆየባቸው አርባ አመታት በዋናነት በወንዶች በብቸኝነት ይካሄድ የነበረና ምንም ዓይነት የሴቶች ተሳትፎ የሌለበት ነው የሚል ነው፡፡ የቤተዘመድ ሽምግልና ጉባኤን በአዎንታዊ መልኩ የሚያዩ ወገኖች ደግሞ ምንም እንኳን በከተሞች አካባቢ ጉዳዮችን በማጓተት ረገድ አንዳንድ ችግሮች እንዳሉ ቢታወቅም የቤተሰብ ሽምግልና ጉባኤ በባህል፣ በሀይማኖትና በማህበራዊ ግንኙነቶች ከፍተኛ ተቀባይነት ያለውና በተለይም በገጠሩ ኅብረተሰብ ዘንድ እንደ አንድ ባህላዊ እሴት የሚታይና በሚገባ እየሠራ ያለ በመሆኑ ያሉበት አንዳንድ ችግሮች ተቀርፈውና ለማስታረቅም ሆነ ፍቺ ለመወሰን በሕጉ አስፈላጊው ጊዜ ተወስኖለት ሊቀጥል ይገባል እንጂ ሙሉ በሙሉ ከሕጉ መሰረዝ ሌላ የተሻለ አማራጭ በሌለበት ሁኔታ የባሰ ችግር እንደሚፈጥር፤ ለቤተዘመድ ጉባኤ የተሰጠው ሥልጣን ለፍ/ቤት በመተላለፉ ብቻ ችግሩ ሙሉ በሙሉ ሊወገድ ይችላል ብሎ መደምደምም እንደማይችል የሚያመለክቱ መከራከሪያዎች አቅርበው ነበር፡፡

ሁለቱንም አመለካከቶች ያራምዱ የነበሩ ወገኖች በተግባር ካጋጠሙ ችግሮችና አዎንታዊ ሁኔታዎች በመነሳት ዝርዝር ምክንያቶችና ማስረጃዎችን ያቀርቡ የነበሩ ሲሆን ለውይይት በተሰራጨው ረቂቅ የቤተሰብ ሕግም የቤተዘመድ ሽምግልና ጉባኤ ሙሉ በሙሉ አላስፈላጊ ነው የሚል አቋም አልተያዘም ነበር፡፡ በመጀመሪያው ረቂቅ መሠረት የቤተዘመድ ሽምግልና ጉባኤ በባልና ሚስት ወይም ከሁለቱ አንዳቸው የፍቺ ጥያቄ ሲያቀርቡ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ የማስታረቅ ሚና ብቻ እንዲኖረው እና የፍቺው ውሳኔ፣ የንብረት ክፍፍል፣ የልጆች አስተዳደግና የመሳሰሉት ጉዳዮች በፍርድ ቤት እንዲከናወኑ ሓሳብ ቀርቦ ነበር፡፡[9] በረቂቁ ላይ በተከታታይ በተካሄዱ ዐውደ ጥናቶች የቤተዘመድ ሽምግልና ጉባኤን በተመለከተ በበርካታ ጭብጦች ላይ የተለያዩ አመለካከቶች ቢንፀባረቁም የቤተዘመድ ሽምግልና ጉባኤ በቤተሰብ ጉዳይ ሚና ሊኖረው ይገባል የሚለው አመለካከት የአብዛኛው ሕብረተሰብ ክፍል እምነት ነበር ማለት ይቻላል፡፡

በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ በመጨረሻ የተወሰደው አቋም የቤተዘመድ ሽምግልና ጉባኤን አስፈላጊነት ሙሉ በሙሉ የሚሽር ባይሆንም መሠረታዊ ለውጥ ተደርጓል፡፡ በተሻሻለው ሕግ መሠረት በባልና ሚስት መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶች ፍቺና ከፍቺ በመለስ ያሉ ተብለው በሁለት ተከፍለዋል፡፡[10] በዚህም መሠረት የፍቺ ጥያቄን የመቀበልና የመወሰን ሥልጣን ለፍርድ ቤቶች ብቻ እንዲሆን የተደረገ ሲሆን የሽማግሌዎች ኃላፊነት ለማስታረቅ ጥረት ማድረግ ብቻ እንጂ ምንም ዓይነት ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን የላቸውም፡፡ የሽማግሌዎች አመራረጥም እንደቀድሞው ሕግ ከባል ወገን ሁለት ከሚስት ወገንም ሁለት በሚል ዓይነት ሳይሆን ባልና ሚስቱ ተስማምተው የመረጡት አንድ ሰው ብቻም ሊሆን ይችላል፡፡ የፍቺ ውጤቶችን በሚመለከትም ምንም እንኳን በራሳቸው ወይም በሽማግሌዎች አማካይነት ስምምነት ለማድረግ የሚችሉ ቢሆንም የመጨረሻ ተፈፃሚነት ያለው ውሳኔ የመስጠት ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት ብቻ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ በአጠቃላይ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ በቤተሰብ ጉዳይ ሽማግሌዎች ሚና እንዳላቸው ቢቀበልም ፍቺን ጨምሮ የሚከሰቱ አለመግባባቶችን በፍትሐዊነት መወሰን የሚቻለው በመደበኛው የፍትሕ ሥርዓት በፍርድ ቤት ነው የሚል አቋም መውሰዱን መገንዘብ ይቻላል፡፡

[9] የቤተሰብ ሕግ የመጀመሪያ ረቂቅ አንቀጽ 89-93
[10] የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 117-122

## 6. ጋብቻ በፍቺ ስለሚፈርስበት ሁኔታና የፍቺ ምክንያቶችን በሚመለከት

በነባሩ የፍትሐብሔር ሕግ መሠረት ጋብቻ ሊፈርስ የሚችልባቸው የተለያዩ ምክንያቶች ሲኖሩ ከእነዚህ አንዱ ፍቺ ነው፡፡ ጋብቻ በፍቺ ምክንያት ሲፈርስ የተለያዩ ውጤቶች ሊያስከትል እንደሚችል ይታወቃል፡፡ ሕጉን ለማሻሻል በተካሄዱ ዐውደ ጥናቶችና ውይይቶች ፍቺንና ምክንያቶቹን በሚመለከት የተለያዩ አከራካሪ ጥያቄዎች የተነሱ ከመሆኑም በላይ የአመለካከት ልዩነቶችም እንደነበሩ መገንዘብ ተችሏል፡፡ ፍቺንና ምክንያቶቹን በሚመለከት ተነስተው የነበሩት ዋና ዋና ጥያቄዎች ጠቅለል ብለው ሲታዩ የሚከተሉት ነበሩ፡፡

ሀ) ጋብቻ በተጋቢዎች ነፃና ሙሉ ፈቃድ ብቻ እንደሚመሰረት ሁሉ ፍቺም ነፃ መሆን ይኖርበታል ወይስ ገደብ ሊደረግበት ይገባል?

ለ) የፍቺ ምክንያቶችን ከባድና ቀላል ብሎ መከፋፈል አስፈላጊ ነውን? ምክንያቶቹን በሙሉ ዘርዝሮ ማስቀመጥስ ይቻላል?

ሐ) የፍቺ ምክንያቶች ከባድና ቀላል ተብለው ሊከፋፈሉ ይችላሉ ከተባለ በአንደኛው ወገን የሚፈፀም እንደ ድብደባ፣ የጋራ ንብረትን ማባከን፣ አዘውትሮ መስከር፣ ያለበቂ ምክንያት ከግብረሥጋ ግንኙነት መታቀብ፣ የአደንዛዥ እጽ ተጠቃሚ መሆን፣ የጭካኔ ተግባር መፈፀም፣ ቀለብ መከልከል ወዘተ የመሳሰሉት ድርጊቶች ከባድ ምክንያቶች ተብለው ሊፈረጁ ይችላሉ ወይ? የከባድነቱ መለኪያ ምንድን ነው? ለምሳሌ ስካር ወይም የጭካኔ ተግባር የሚለው ጥቅል አነጋገር ለትርጉም ሰፊ በር የሚከፍትና ለአፈጻጸም ችግር የሚፈጥር አይሆንም ወይ?

መ) ጋብቻ ጥፋት በሆነ ከባድ የፍቺ ምክንያት እንዲፈርስ ከተወሰነ ለመፍረሱ ምክንያት የሆነው ወገን ከንብረቱ ላይ በመቀጫ መልክ ካሳ መክፈል አለበት ወይ?

ሠ) የፍቺን ምክንያት ከንብረት ክፍፍል ጋር ማያያዙ እስከዛሬ እንደታየው ለፍቺ ውሳኔ በቶሎ አለመስጠት ምክንያት አይሆንም ወይ?

ረ) ከባድ የፍቺ ምክንያቶች ባጋጠሙ ጊዜ ጉዳዩ በመጀመሪያ በቤተዘመድ ሽምግልና ጉባኤ በእርቅ እንዲታይ ዕድል መስጠት ያስፈልጋል ወይ?

የሚሉና ሌሎችም ተዛማጅ ጥያቄዎች ናቸው፡፡

ከዚህ በላይ በተገለጹት ጥያቄዎች ላይ በተደረጉ ውይይቶች የተለያዩ አመለካከቶች ተንፀባርቀዋል፡፡ በውይይቶች ተሳታፊ የነበሩና በወቅቱ በዳኝነት ሥራ ላይ የነበሩ እንዲሁም በጥብቅና ሥራ ላይ የነበሩ ተሳታፊዎች የጉዳዩን አስቸጋሪነት በማንሳት በእያንዳንዱ ምክንያት ላይ ዝርዝር መለኪያዎች ካልተቀመጡ በተግባር ሲተረጎም አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል የሚል ሓሳብ ይሰነዝሩ ነበር፡፡ ፍቺን በሚመለከት በተደረገው ሰፊ የሕዝብ ውይይት ባልና ሚስት በራሳቸው ፈቃድ የተጋቡ እስከሆነ ድረስ በጋብቻ ለመቀጠልና አብረው ለመኖር ካልፈለጉ በራሳቸው ስምምነት መለያየት መቻል አለባቸው፣ፍ/ቤቱም የፍቺ ስምምነት ከቀረበለት ወይም አንደኛው ወገን ከጠየቀ ጉዳዩን ተቀብሎ ማጽደቅና ማስረጃ መስጠት እንጂ የማስታረቅና የማከራከር ጉዳይ ውስጥ መግባት የለበትም የሚል ክርክር የነበረ ሲሆን፤ በሌላ ወገን ደግሞ የጋብቻ መፍረስ እንደቀላል ነገር መታየት የለበትም፣ ፍቺ ከጋብቻው የተገኙትን ልጆች መብት በሚያስጠብቅ ሁኔታ በሕግ አግባብ ሊደረግ ይገባል እንጂ ባል ሚስቱን ወይም ሚስት ባልዋን አልፈልግም ስላሉ ብቻ ጋብቻ ይፍረስ ማለት ትክክል አይደለም የሚል አመለካከት ነበር፡፡ ለሕዝብ ውይይት በቀረበው ረቂቅ የተንፀባረቀውም ይኸው በፍትሐብሔር ሕጉ የነበረው ሁለተኛው አመለካከት ነበር፡፡[11]

ነባሩ የፍትሐብሔር ሕግ የፍቺ ምክንያቶችን ከባድ ምክንያቶችና ሌሎች /ቀላል ምክንያቶች/ ብሎ በሁለት ይከፍላቸዋል፡፡ ከባድ የሚባሉት ከባልና ሚስት በአንደኛው ወገን ጥፋት የሚመነጩ ወይም የማናቸውም ወገን ጥፋት ሳይኖርበት የሚከሰቱ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የፍቺ ምክንያቶችን ቀላልና ከባድ ብሎ የመከፋፈልን ጉዳይ በተመለከተ ምክንያቶች ከሚያስከትሉት

[11] የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ የመጀመሪያ ረቂቅ 1991 አንቀጽ 78

ውጤት አንፃር ተገቢ እንደሆነና በተለይ ከባልና ሚስት በአንደኛው ወገን ጥፋት ላይ የተመሰረቱ የከባድ ምክንያቶች ዝርዝር ሰፋ እንዲልና በፍትሐብሔር ሕጉ ከተዘረዘሩት የዝሙት ተግባርና አድራሻውን ሳያሳውቅ ከሁለት ዓመት በላይ ከቤት መጥፋት (መኮብለል) ውጭ ሌሎችንም በመጨመር ሕጉ መሻሻል እንዳለበት ከልዩ ልዩ የኀብረተሰብ ክፍሎች የተለያዩ አመለካከቶች ተሰንዝረው ነበር። ለውይይት ቀርቦ የነበረው ረቂቅ የቤተሰብ ሕግ (ይህን አስተሳሰብ በመቀበል ይመስላል) ከባልና ሚስት አንዱ በሌላው ላይ የጭካኔ ተግባር መፈፀም እንደ አንድ ተጨማሪ ከባድ የፍቺ ምክንያት እንዲካተት አድርጐ ነበር።[12]

በሌላ በኩል ደግሞ የፍቺ ምክንያቶችን ከባድና ቀላል ብሎ መከፋፈል ችግር ሊኖረው እንደሚችል የቀረቡ መከራከሪያዎች ነበሩ። በተለይም ከባልና ሚስት በአንደኛው ጥፋት ላይ የተመሰረተ ከባድ የፍቺ ምክንያት አጥፊውን ወገን በንብረት ክፍፍል ላይ ተቀጭ ስለሚያደርግና ከባድ ባልሆነ ምክንያትም ፍቺ የጠየቀው ወገን በተመሳሳይ ቅጣት ስለሚጣልበት በንብረት ላለመቀጣት ብቻ በደል እየደረሰበትም ፍቺ ላይጠይቅ ይችላል። ይህም ጋብቻውን ጠጋግኖ ለማቆየት የሚደረግ ሙከራ ከሚሆን በስተቀር ለተጋቢዎች ጠቃሚ ስላልሆነ ባልና ሚስት በጋብቻው መቀጠል ካልፈለጉ ፍቺ እንዲደረግ መፍቀድና የንብረት ክፍፍልንም እኩል ማድረግ እንጂ የቅጣት ሓሳብ መኖር የለበትም፣ በተጨማሪም በጥፋት ላይ የተመሰረቱ የሚባሉ ከባድ የፍቺ ምክንያቶችን በሙሉ ዘርዝሮ ለማስቀመጥ አስቸጋሪ ከመሆኑም በላይ በተለይ አንዳንዱን ምክንያት የከባድነቱን ደረጃ መወሰኑ አስቸጋሪ ነው፣ ስለዚህ የፍቺ ጥያቄ ሲቀርብ ምክንያት እንዲኖር ማስገደድም ሆነ ምክንያቶችን በደረጃ መከፋፈል አስፈላጊ አይደለም የሚል አመለካከት ነበር።

ይህ ክርክር በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ በመጨረሻ እልባት እንዲያገኝ የተደረገው ከሞላ ጐደል የኋለኛውን አስተሳሰብ በመከተል ነው።[13] በነባሩ የፍትሐብሔር ሕግ ሚስት ባሏን ወይም ባል ሚስቱን አልፈልግም በማለት ብቻ ጋብቻ እንዲፈርስ አይፈቅድም ነበር። በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ መሠረት ፍቺ በሁለት መንገድ ሊፈፀም ይችላል። አንደኛው መንገድ ባልና ሚስት በስምምነት ለመፋታት ተስማምተው የፍቺ ስምምነታቸውንና ፍቺው የሚያስከትለውን ውጤት በጽሁፍ ለፍርድ ቤት አቅርበው እንዲፀድቅላቸው የሚያደርጉበት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከባልና ሚስት አንደኛው ወይም ሁለቱም በጋራ ጋብቻው በፍቺ እንዲፈርስ ለፍርድ ቤት ጥያቄ የሚያቀርቡበት አሠራር ነው።

በተሻሻለው ሕግ መሠረት ባልና ሚስት በስምምነት ለመፋታት ያደረጉት ስምምነት እንዲፀድቅላቸው በሚያቀርቡት ጥያቄም ሆነ ጋብቻው በፍቺ እንዲፈርስ ለፍ/ቤት አቤቱታ በሚያቀርቡበት ጊዜ ለመፋታቱ ምክንያት የሆነውን ጉዳይ እንዲጠቅሱ አይገደዱም። ይህም ማለት ፍቺ ለመወሰን የግድ ምክንያት ማቅረብ አስፈላጊ አለመሆኑን ነው። ስለሆነም በቀድሞው ሕግ የፍቺ ምክንያቶችን ከባድና ሌሎች ምክንያቶች በማለት ተደንግጐ የነበረውንና እንደየምክንያቱ ሁኔታ ፍቺው በንብረት ክፍፍል ላይ ያስከትል የነበረው ውጤት በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ቀሪ ሆኗል። ይሁን እንጂ የተሻሻለው ሕግ ከቀድሞው ሕግ የወረሰው አንድ ነገር አለ። ይኸውም ጋብቻ በፍቺ በሚፈርስበት ጊዜ ከባልና ሚስት አንዱ ለፍቺው ምክንያት የሆነውን በደል ፈጽሞ የተገኘ እንደሆነ በሌላው ተጋቢ ላይ ለደረሰው ጉዳት በዳዩ ተመጣጣኝ ካሳ እንዲከፍል ፍ/ቤት ሊወስንበት እንደሚችል የተደነገገው ነው።[14] በሌላ አነጋገር ከባልና ሚስት አንደኛው ወይም ሁለቱ በአንድነት ጋብቻው በፍቺ እንዲፈርስ ጥያቄ በሚያቀርቡበት ጊዜ ተበድያለሁ የሚለው ወገን ካሳ እንዲከፈለው ከፈለገ ለፍቺው ምክንያት የሆነውን በደል መግለጽ አለበት ማለት ነው።

---

[12] የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ የመጀመሪያ ረቂቅ 1991 አንቀጽ 83(ሐ)

[13] የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 77(3)፣ 81(2)

[14] የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 84 (ይህ አንቀጽ መጨረሻ ላይ የተጨመረ መሆኑን ፀሐፊው ያስታውሳል::)

## 7. ሌሎች ልዩ ልዩ ጉዳዮች

### 7.1 ቅድመ ጋብቻ የጤና ምርመራን ሕጋዊ ግዴታ ስለማድረግ

ጋብቻ ለመፈፀም መሟላት ያለባቸው ሕጋዊ ሁኔታዎች ምን እንደሆኑ በነባሩ የፍትሐብሔር ሕግም ሆነ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ በተመሳሳይ አኳኋን ተደንግገዋል፡፡ የቤተሰብ ሕጉ የመጀመሪያ ረቂቅ ለሕዝብ ውይይት በቀረበበት ወቅት አንድ ወንድና አንዲት ሴት ለመጋባት ሲወስኑ ከጋብቻ በፊት የጤና ምርመራ በማድረግ ጤነኛ መሆናቸውን የሚያረጋግጡበት ሥርዓት እንደ አንድ የጋብቻ ቅድመ ሁኔታ በቤተሰብ ሕግ ሊካተት ይገባል የሚል አስተያየት በአንዳንድ ወገኖች ቀርቦ ነበር፡፡ በነዚህ ወገኖች አስተሳሰብ ከጋብቻ በፊት የጤና ምርመራ ማድረግን ሕጋዊ ግዴታ ማድረግ ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው፡፡ ይህንኑ መነሻ በማድረግም በረቂቅ ሕጉ ላይ በተደረጉ ውይይቶች ኤች.አይ.ቪ. ኤድስን ጨምሮ ለሕይወት አደገኛ በሆነ ተላላፊ በሽታ የተያዙ ሰዎች የሚፈጽሙት ጋብቻ ውጤት አስከፊ ስለሚሆንና በተለይም የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ በሽታ መስፋፋት በኅብረተሰቡ ላይ በማድረስ ላይ ያለውን ጉዳት ለመቀነስና በጋብቻ ምክንያት ለበሽታው የሚጋለጡ ሰዎችን መብት ለመጠበቅ ሲባል አስገዳጅ ቅድመ ጋብቻ የጤና ምርመራ በቤተሰብ ሕጉ ሊካተት ይገባል የሚሉ ሓሳቦችና ክርክሮች ቀርበው ነበር፡፡

ከዚህ አስተሳሰብ በተቃራኒው የቆሙ ወገኖች ደግሞ ጉዳዩን ከሌላ አቅጣጫ በመመልከት የቀረበውን ሓሳብ ተቃውመዋል፡፡ ሓሳቡን በተቃወሙ ወገኖች እምነት ይህን መሰል አስተሳሰብ በቤተሰብ ሕጉ ለማካተት መሞከር ሕገመንግሥታዊ ካለመሆኑም በላይ አድሎአዊ ይሆናል፡፡ ተጋቢዎች ቅድመ ጋብቻ ምርመራ ካደረጉ በኋላ አንዳቸው ወይም ሁለቱም ሊድን በማይችል በሽታ የተያዙ መሆኑ ቢረጋገጥ ጋብቻ እንዳይፈጽም መከልከል ይቻላልን? ጋብቻ ማንም ሰው ሊፈጽመው የሚችል ተፈጥሮአዊ መብት በመሆኑና በሕገ መንግሥቱ መሠረት በጋብቻ ልዩነት ማድረግ እንደማይቻል የተደነገገ በመሆኑ አስገዳጅ የጤና ምርመራን በቅድመ ሁኔታነት ማስቀመጥ የዜጐችን መብት በቀጥታ ይጻረራል በማለት ተከራክረዋል፡፡ በመጨረሻ የተወሰደው አቋም ምንም እንኳን ተጋቢዎች አስፈላጊውን የጤና ምርመራ አስቀድመው በማድረግ ከተለያዩ ተላላፊ በሽታዎች ነፃ መሆናቸውን አውቀው መጋባታቸው ለራሳቸውና ለሚወልዷቸው ልጆች ጤንነት አስፈላጊና በአጠቃላይ ለኅብረተሰብ ጤና አጠባበቅ ጠቃሚ መሆኑ ባያከራክርም በሕግ ከማስገደድ ይልቅ ሕዝቡን በማስተማር ቢሆን እንደሚሻልና ለአፈፃፀም አስቸጋሪ እንደሚሆን በመታመኑ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ውስጥ እንደሕግ ድንጋጌ (legal provision) እንዲካተት አልተደረገም፡፡

### 7.2 ባልና ሚስት ሊሰማሩ የሚችሉበትን የሙያ (የሥራ) ዘርፍ በሚመለከት (Occupation of Spouses)

ባልም ሆነ ሚስት የመረጡትን የሙያ ወይም የጥበብ ሥራ ማከናወን እንደሚችሉ ነባሩ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 645 ያመለክታል፡፡ ይሁን እንጂ ከባል ወይም ከሚስት አንዳቸው የተሰማሩበት ሥራ ለትዳራቸው ወይም ለቤተዘመዳቸው መልካም አኗኗር የማይጠቅም ከሆነ የአንደኛውን የሙያ ሥራ ሌላኛው ለመቃወም እንደሚችል በዚሁ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 2 ሥር ተደንግጓል፡፡ የቤተሰብ ሕጉን በማሻሻሉ ሂደት ይህ በቀድሞው ሕግ የነበረው አስተሳሰብ በሚሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ሊካተት ይገባል ወይ? ተቃውሞ ማድረግ የሚቻልበት ሥርዓት የሚኖር ከሆነ ምክንያቱ ተዘርዝሮ ሊቀመጥ ይችላልን? በሚሉት ጥያቄዎች ላይ ሰፊ ውይይትና ክርክር ተደርጐባቸዋል፡፡

ለሕዝብ ውይይት በተዘጋጀው ረቂቅ የቤተሰብ ሕግ ባል ወይም ሚስት የተሰማሩበትን የሙያ ወይም የሥራን ዓይነት ከሁለት አንደኛው ለትዳራችን አይጠቅምም በማለት የመቃወም አስተሳሰብ በፍትሐብሔር ሕጉ ከነበረው በጠበበ ሁኔታ እንዲቀጥል ሓሳብ ቀርቦ ነበር፡፡ ለውይይት በቀረበው የመጀመሪያው ረቂቅ ላይም ተካቶ ነበር፡፡[15] በረቂቁ ላይ በተካሄዱ ውይይቶች እንደታየው በሕገ መንግሥቱ መሠረት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ

---

[15] የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ የመጀመሪያ ረቂቅ 1991 አንቀጽ 63 (2)

*መተዳደሪያውን፣ ሥራውንና ሙያውን የመምረጥ መብት ስላለው በጋብቻ ምክንያት የሙያ ሥራን የመቃወም ድንጋጌ ማስቀመጥ በሕገ መንግሥት የተረጋገጠን መሠረታዊ መብት የሚጻረር ስለሆነ ገደብ ሊኖር እንደማይገባና ገደቡን ለማስቀመጥ ሕጋዊ ምክንያት የሚኖር ቢሆን እንኳን ተቃውሞ ሊነሳባቸው የሚችሉ ምክንያቶችን በዝርዝር ማስቀመጥ ካልተቻለ በአፈጻጸም ረገድ ችግር ሊያስከትል ስለሚችል ጉዳዩን በሕግ ከመደንገግ ይልቅ ተጋቢዎች የተሰማሩበት ወይም ሊሰማሩበት ያሰቡት የሙያ ሥራ ለራሳቸውና ለቤተሰባቸው መልካም አኗኗር የሚጠቅም ወይም የማይጠቅም መሆኑን በራሳቸው ቢወስኑ እንደሚሻል በመታመኑ ከተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ እንዲሰረዝ ተደርጓል፡፡*

### 7.3 *ጋብቻ እንዲፈርስ የፍቺ ጥያቄ ቀርቦ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት በልጆች አያያዝና በንብረት አጠባበቅ ላይ የሚተላለፉ ጊዜያዊ ውሳኔዎችን በሚመለከት*

*ጋብቻ ከሚፈርስባቸው የተለያዩ ምክንያቶች አንዱ ፍቺ እንደሆነ ቀደም ሲል ተመልክተናል፡፡ የፍቺ ጥያቄ ከቀረበ በኋላ ፍቺ እስከሚወሰን ድረስ የተወሰነ ጊዜ መውሰዱ የማይቀር ነው፡፡ ፍቺ ከተወሰነም በኋላ ቢሆን የፍቺ ውጤቶችን ለመወሰን ጊዜ ይጠይቃል፡፡ ጋብቻ በሚፈርስበት ሂደት ላይ እያለ በተለይ የሕፃናትን አስተዳደርና አያያዝ በተመለከተ የቤተሰብ ሕጉ ምን ዓይነት ድንጋጌዎች ሊኖረው ይገባል? የልጆችን የዘለቄታ አኗኗር በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ የልጆች አስተያየት የሚጠየቅበት ሁኔታ ሊኖር ይገባል? ከእናት ወይም ከአባት ጋር መቆየት ያለባቸውን ሕፃናት በዕድሜ ወይም በሌላ ሁኔታ በመለየት በሕግ መደንገግ ያስፈልጋልን? ፍቺ ከመወሰኑ በፊት ባልና ሚስት ተለያይተው መቆየት ካለባቸው በጋራ መኖሪያቸው የመቆየት መብት ለማን ሊሆን ይገባል? ለባል ወይስ ለሚስት? እነዚህን ጥያቄዎች በተመለከተ ፍርድ ቤቶች የሚሰጧቸው ጊዜያዊ ትዕዛዞች ምን ምን ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ ሊያስገቡ ይገባል? በሚሉ ጥያቄዎች ላይ የቤተሰብ ሕጉን ለማሻሻል በተካሄዱ ውይይቶች የተለያዩ ሰፊ የአመለካከት ልዩነቶች ተንጸባርቀዋል፡፡*

*በነባሩ የፍትሐብሔር ሕግ መሠረት ጋብቻ የሚፈርስባቸው ምክንያቶች ሲያጋጥሙ የፍቺ ጥያቄ የሚቀርበው ለቤተዘመድ ሽምግልና ዳኞች እንደነበር ይታወቃል፡፡ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ግን ጥያቄው መቅረብ ያለበት ለፍ/ቤት ብቻ ነው፡፡ በቀድሞው ሕግ የፍቺ ክርክሩ በመታየት ላይ እያለ የጋራ ንብረት አጠባበቅንና የልጆችን አኗኗር (ቀለብ፣ ትምህርት፣ ጤና ወዘተ) በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ የቤተዘመድ ሽምግልና ዳኞች ጊዜያዊ ውሳኔዎችን ይሰጡ እንደነበር ይታወቃል፡፡ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ እንዲህ ዓይነት ጉዳዮች ቀርበው ትዕዛዝ የሚሰጥባቸው በፍርድ ቤት እንደሆነ ተመልክቷል፡፡*

*ፍርድ ቤት ጊዜያዊ ውሳኔዎችን በሚሰጥበት ጊዜ በተለይ ባልና ሚስት ተለያይተው መቆየት ካለባቸው ከጋራ መኖሪያቸው መውጣት ያለበት ማነው የሚለው ጥያቄ ከፍተኛ ክርክር ያስነሳ ነበር፡፡ በአንድ ወገን የነበረው አመለካከት በፍቺ ክርክር ወቅት ጉዳት ላይ የሚወድቁት ሴቶችና ሕጻናት በመሆናቸው ቤቱን ለቆ መውጣት ያለበት አባወራው መሆን እንዳለበትና ይህም በሕጉ በግልጽ ሊደነገግ ይገባል የሚል ነበር፡፡ የሕጻናትን አያያዝ በሚመለከትም ዕድሜያቸው ከአምስት ዓመት በታች የሆኑ ሕጻናት የግድ ከእናታቸው ጋር መቆየት እንዳለባቸው ቀደም ሲል በፍትሐብሔር ሕጉ ተደንግጎ የነበረው እንዲቀጥል ለውይይት በቀረበው ረቂቅ ሓሳብ ቀርቦ ነበር፡፡*

*በሌላ ወገን የነበረው ክርክር ደግሞ አባወራው ከቤት ወጥቶ እንዲቆይ አስቀድሞ በሕግ መወሰን አንዱን ወገን ሁልጊዜም የችግሩ መንስኤና ጥፋተኛ አድርጎ መፈረጅ ስለሆነ ተቀባይነት የሌለው አስተሳሰብ ነው፣ የሕጻናትን አያያዝ በተመለከተም ጉዳዩ መታየት ያለበት ለሕጻናት አያያዝና ጥቅም የሚበጀው የትኛው ነው ከሚል መሆን አለበት የሚል ሲሆን፣ ከጋራ መኖሪያ የሚወጣውንና ስለሕጻናት አያያዝ አስቀድሞ በሕግ መገደቡ ጠቃሚ እንዳልሆነ ክርክሮች ቀርበዋል፡፡ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ለነዚህ ጥያቄዎች የሰጠው ምላሽ በሁለቱ መካከል የሚታይና ከሞላ ጐደል የኋለኛውን ክርክር የሚያጠናክር ሆኖ ለፍርድ ቤቶች ሰፊ ሥልጣን የሰጠ ነው፡፡ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ* 82(6) *ላይ እንደተመለከተው ፍርድ ቤቱ ባልና ሚስቱ ስለሚተዳደሩበትና ስለሚኖሩበት ሁኔታ፣ ስለልጆቻቸው አጠባበቅ፣*

ስለሚኖሩበት ሥፍራና ስለአኗኗራቸው እንዲሁም ስለንብረታቸው አስተዳደር ትዕዛዝ በሚሰጥበት ጊዜ ከሁለቱ ተጋቢዎች የአንዳቸው ከጋራ መኖሪያቸው መውጣት የግድ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ የጋራ መኖሪያቸውን ለቆ ቢወጣ የባሰ ጉዳት የሚደርስበት ወገን የትኛው መሆኑን እንዲሁም የልጆቻቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ አመቺ የሆነውን ሁኔታ ሁሉ ከግምት ውስጥ ማስገባት እንዳለበት ብቻ በማመልከት ውሳኔውን ለፍርድ ቤት በመተው ደንግጓል፡፡

### 7.4 አንዲት ሴት ጋብቻዋ ከፈረሰ በኋላ ሌላ ጋብቻ ለመፈፀም መቆየት ስለሚኖርባት ጊዜ (Period of Windowhood)

በነባሩ የፍትሐብሔር ሕግ መሠረት አንዲት ሴት አስቀድሞ የነበራት ጋብቻ በሕጋዊ መንገድ ከፈረሰ በኋላ ሌላ ጋብቻ ከመፈጸሟ በፊት የተወሰነ ጊዜ እንድትቆይ የሚያስገድድ ድንጋጌ ነበር፡፡ ይህ ሁኔታ በሕጉ በብቸኝነት ለመኖር የተወሰነ ጊዜ በመባል ይታወቃል፡፡ በሕጉ መሠረት አንዲት ሴት አስቀድሞ የነበራት ጋብቻ ከቀረ በኋላ አንድ መቶ ሰማኒያ ቀን ካላለፈ በቀር እንደገና ለማግባት አትችልም፡፡ ይህ የጊዜ ገደብ እንደ አንድ የጋብቻ ቅድመ ሁኔታ የተቀመጠ በመሆኑ ይህን ገደብ ተላልፎ ጋብቻውን ያስፈጸመ የክብር መዝገብ ሹም፣ ለጋብቻው ፈቃደኛ የሆኑ ተጋቢዎችና ምስክሮች ሁሉ በወንጀል ሊቀጡ እንደሚችሉ ተደንግጎ ነበር፡፡[16]

የቤተሰብ ሕጉን በማሻሻሉ ሂደት በተደረጉ ውይይቶች ይህ ገደብ በሚሻሻለው ሕግ ተካቶ ሊቀጥል አይገባም በሚሉና መኖሩን በሚደግፉ ወገኖች መካከል ክርክር አስነስቶ ነበር፡፡ የድንጋጌው ዓላማ አስቀድሞ ከነበረው ጋብቻ የተፀነሰ ልጅ ካለ የልጁን አባትነት ጥያቄ አስመልክቶ ሊነሳ የሚችለውን ችግር ከወዲሁ ለማስወገድና የልጆችን መብት ለማስጠበቅ እንደሆነና በተግባርም ያስከተለው ችግር ባለመኖሩ በሕጉ መካተቱ ተገቢ እንደሆነ በመውሰድ በፍትሐብሔር ሕጉ የነበረው ድንጋጌ ለውጥ ሳይደረግበት ለሕዝብ ውይይት በቀረበው ረቂቅ የቤተሰብ ሕግ ተካቶ ነበር፡፡[17] በሌላ በኩል የገደቡን በሕጉ መካተት በሚቃወሙ ወገኖች እምነት ድንጋጌው አድሎአዊ፣ ሴቶችን የሚበድል፣ ከዘመናዊ የሳይንስ ዕውቀት ጋር የማይሄድና ኋላ ቀር አስተሳሰብ ነው፤ ምክንያቱም በዘመናዊና ሣይንሳዊ ዘዴ የጽንስ መኖር አለመኖርን በቀላሉ ማረጋገጥ የሚቻል መሆኑ እየታወቀ ሴቶች ሌላ ጋብቻ ለመፈጸም ስድስት ወራት እንዲጠብቁ በሕግ ማስገደድ ለጋብቻ የተሰጠውን መብት ያጣብባል የሚል ክርክር ነበር፡፡

የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ለተነሱት ክርክሮች የሰጠው ምላሽ ሁለቱንም አመለካከት ያካተተ ነው ማለት ይቻላል፡፡ የተሻሻለው ሕግ አንዲት ሴት መጀመሪያ ጋብቻዋ ከፈረሰ በኋላ ሌላ ባል ለማግባት አንድ መቶ ሰማኒያ ቀናት በብቸኝነት መቆየት እንዳለባት በመርህ ደረጃ ይቀበላል፡፡ ይሁን እንጂ ሴትዮዋ እርጉዝ አለመሆኗ በሕክምና ከተረጋገጠ ጊዜውን ለመጠበቅ እንደማትገደድ አዲስ ሁኔታ በሕጉ ተጨምሯል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሴትዮዋ በብቸኝነት ለመቆየት የተወሰነውን ጊዜ እንዳትጠብቅ የተለያዩ ሁኔታዎችን በማየት ፍርድ ቤት ሊወስን እንደሚችል ተደንግጓል፡፡[18]

### 7.5 በባልና ሚስት መካከል በሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ስለሚፈጠሩ ችግሮች

ጋብቻ በተጋቢዎች የግልና ማህበራዊ ግንኙነቶች ላይ የሚያስከትላቸው በርካታ ውጤቶች አሉ፡፡ ከነዚህም መካከል ባልና ሚስት አብረው ለመኖር የሚገደዱ መሆኑ፣ አንዱ ለሌላው ታማኝ የመሆን፣ በኑሮአቸው አመራር መተጋገዝ፣ መከባበርና መደጋገፍ ያለባቸው መሆኑና ለጤናቸው አደገኛ ካልሆነ በስተቀር ደንበኛውን የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት መፈፀም ያለባቸው መሆኑ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ የቤተሰብ ሕጉን በማሻሻሉ ሂደት በነዚህ ጉዳዮች በተለይም ከግብረ ሥጋ ግንኙነት ጋር በተያያዘ በባልና ሚስት መካከል የሚፈጠሩ ችግሮች የሚያስከትሉትን ውጤት በተመለከተ ከፍተኛ አወዛጋቢ የአመለካከት ልዩነት ተፈጥሮ ነበር፡፡ በአንዳንድ ወገኖች እምነት ባልና ሚስት ደንበኛውን የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት እንዲያደርጉ

---

[16] የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 620

[17] የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ የመጀመሪያ ረቂቅ 1991 አንቀጽ 37

[18] የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 16

የሚገደዱ ቢሆንም ለጤንነት ጎጅ በሆነ ሁኔታ ወይም ያለፍላጎት የሚደረግ ግንኙነት የወንጀል ተጠያቂነት ሊያስከትልና ሊያስቀጣ እንደሚገባና በጋብቻ ውስጥ የአስገድዶ መድፈር (Marital Rape) የተከለከለ ስለመሆኑ በሕጉ በግልጽ እንዲካተት የሚል አመለካከት ነበራቸው። ለሕዝብ ውይይት በቀረበው ረቂቅ የቤተሰብ ሕግም በፍትሐብሔር ሕጉ የነበረውን ድንጋጌ በማሻሻል "**ለጤና አደገኛ በሆነና ከደንበኛው የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ተቃራኒ በሆነ መንገድ የተፈጸመ ግንኙነት ተጎጅው በሚያቀርበው ክስ መሠረት በወንጀል ያስቀጣል**" የሚል አንቀጽ ተካቶ ነበር።[19] ተጋቢዎች አብረው በሚኖሩበት ጊዜ ሊያደርጉ የሚገባቸውን ግንኙነት የፍትሐብሔር ሕጉ ከማመልከቱ በቀር ተቃራኒ በሆነ መንገድ ተፈጽሞ ቢገኝ የሚያስከትለው ውጤት ባለመገለጹ ድንጋጌው ተፈጻሚነት የሌለው ሆኖ ስለቆየ ማሻሻያው ማስፈለጉ ለረቂቁ በተዘጋጀው ማብራሪያ ላይ ተገልጧል።

በሌላ በኩል ባልና ሚስት የሚያደርጉትን ግንኙነት በተመለከተ ከባህል፣ ከሀይማኖትና ከሞራል አኳያ የግንኙነቱ ወሰን ምን መሆን እንዳለበት በፍትሐብሔር ሕጉ የተመለከተውን ማስቀመጡ አግባብነት ቢኖረውም የወንጀል ኃላፊነት ያስከትላል ከተባለ በማስረጃ ለማረጋገጥና የወንጀል አድራጊውን ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ ማስረዳት አስቸጋሪ ከመሆኑም በላይ ጋብቻውን በጽኑ የሚጐዳ፣ ከቅጣት በኂላ ፍቺን የሚያስከትል፣ በባልና ሚስት መካከልም የጠላትነት ስሜት የሚፈጥርና ውጤቱም የቤተሰብ መፍረስና መበተን ከሚሆን በስተቀር ሌላ ጥቅም አይኖረውም የሚል ተቃውሞ አስከትሎ ነበር። የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ የወሰደው አቋም የኂለኛውን አስተሳሰብ በመደገፍ በመጀመሪያው ረቂቅ የቀረበውን የወንጀል ቅጣት ሀሳብ በመሰረዝ ከሞላ ጎደል በፍትሐብሔር ሕጉ የነበረው አስተሳሰብ እንዲቀጥል አድርጓል። በዚህም መሠረት ባልና ሚስት አብረው ለመኖር የሚገደዱ መሆኑን ለጤናቸው አደገኛ ካልሆነ በቀር ከጋብቻ የሚጠበቀውን መደበኛውን የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም እንዳለባቸውና ይህን የሚቃረን ማናቸውም ስምምነት ውጤት እንደማይኖረው በሕጉ አንቀጽ 53 ላይ ተደንግጓል።

## 7.6 የማህፀን ማከራየትን ጉዳይ በቤተሰብ ሕጉ ስለማካተት (Hiring of womb)

በመካንነት ችግርም ሆነ በሌላ በተለያየ ምክንያት ማርገዝ ያልቻሉ ሴቶች የሌላን ወላድ ሴት ማህጸን በመጠቀም (በመከራየት) የልጅ እናትና አባት መሆን በአንዳንድ አገሮች የተለመደ አሠራር ሆኗል። በዚህም ምክንያት ከአባትነት ወይም እናትነት ጥያቄዎች ጋር በተያያዘ የሚነሱ ችግሮችን ለማስወገድ አንዳንድ አገሮች በሕጋቸው ውስጥ ይህን ጉዳይ በሚመለከት ድንጋጌዎች እያስገቡ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል።

ይህ ጉዳይ በአገራችን የቤተሰብ ሕግ ውስጥ ሊካተት ይገባል ወይ? በሚለው ጥያቄ ላይ የተለያዩ አመለካከቶች መኖራቸውን በጉዳዩ ላይ ከተካሄዱ ውይይቶች ለመገንዘብ ተችሏል። በአንድ በኩል ያለው አመለካከት መውለድ የምትችልን ሴት ማህፀን በመጠቀም ልጅ መውለድ ለማይችሉ ሰዎች ልጅ ማግኘት የሚያስችል ዘመናዊ የሕክምና ዘዴ በመሆኑና በአገራችንም ወደፊት ጥያቄው መነሳቱ ስለማይቀር[20] በቤተሰብ ሕጉ ይህን የሚመለከት ድንጋጌ መስፈሩ አስፈላጊ ነው የሚል ሲሆን በሌላ በኩል የነበረው አስተሳሰብ ደግሞ የማህፀን ማከራየት ተግባር በተፈቀደባቸው አገሮችም እንደ ገቢ ማግኛ ንግድ እየታየ በመምጣቱ ችግር አስከትሏል፣ ስለዚህ በሚወለዱ ልጆች ላይ ችግር ስላለው ይህ ዓይነቱ አከራካሪ ጉዳይ በቤተሰብ ሕጉ ውስጥ መካተት የለበትም የሚል ነበር። ይህን ሓሳብ በመደገፍም ሆነ በመቃወም ሀሳባቸውን ያቀርቡ የነበሩ በእርግጥ ስለጥቅሙም ሆነ ጉዳቱ የሚያቀርቡት ዝርዝርና የተጨበጠ ማስረጃ አልነበረም። በመጨረሻ የጸደቀው የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግም ይህን ጉዳይ አላካተተም።

[19] የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ የመጀመሪያ ረቂቅ 1991 አንቀጽ 59(4)

[20] በአገራችንም በአሁኑ ጊዜ አልፎ አልፎም ቢሆን እንደዚህ መሰል ሁኔታዎች ስለመከሰታቸው በወሬ ደረጃ ይሰማል።

## ማጠቃለያ

ከዚህ በላይ እንደተገለፀው የቤተሰብ ሕጉን ለማሻሻል የሚረዱ ሓሳቦችን ለማሰባሰብ በተከታታይ በተካሄዱና የልዩ ልዩ ኅብረተሰብ ክፍሎች ተወካዮች በተሳተፉባቸው ዐውደ ጥናቶችና ኮንፍረንሶች አከራካሪ ጉዳዮች በደረጃ ተካፍለው ቀርበው ተጨማሪ ውይይቶች ከተካሄዱ በኂላ በአብዛኛዎቹ ጉዳዮች ላይ መግባባት የተደረሰባቸው ሲሆን በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ደግሞ ሓሳቦችን ማቀራረብ አልተቻለም ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት ከፍተኛ የሆነ የአመለካከት ልዩነት ባስከተሉ ጉዳዮች ላይ የተዘጋጀው የመጨረሻ ረቂቅ ሕግ አማራጭ ሓሳቦችን በሚያሳይ መልኩ ተዘጋጅቶ ለሕግ አውጭው አካል እንዲቀርብ ሆኖ ሕጉ አሁን የያዘውን መልክ ይዞ ሊወጣ ችሏል፡፡ የቤተሰብ ሕጉ በሥራ ላይ ከዋለ በርካታ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ ሕጉን በማሻሻሉ ሂደት ተነስተው የነበሩ አከራካሪ ጉዳዮችና በተሻሻለው ሕግ የተሰጣቸው ምላሽ አጥጋቢነት የሚፈተሸው ሕጉ በሥራ ላይ ሲውል ነው፡፡ ሕጉ በተግባር ሲተረጎም ያስገኘው ፋይዳ ወይም ያስከተላቸው ያልተገመቱ ሌሎች ችግሮች ቢኖሩ በመስኩ በሚደረጉ ጥናቶች ተለይተው ሊወጡ ይገባል፡፡ ይህ ጽሁፍም በዚህ መንገድ ለሚደረጉ ጥናትና ምርምሮች ጠቃሚ አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ ይታመናል፡፡ ■